

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት

## የ2000 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት



ሐምሌ/ 2000

<u>ባሕር ዳር</u>

# 1. መግቢያ

በ2000 በጀት አመት የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ያለውንና በበጀት አመቱ ሊያገኝ የሚችለውን ሰብአዊና ቁሳዊ የማስፈፀሚያ ሀብት መሠረት በማድረግ በተለያዩ ፈፃሚ አካላት ሊተገበር የሚችል ዕቅድ በማዘጋጀት ፈጻሚ ኣካላት በስፋት በአፈጻጸሙ እንዲሳተፉ አድርጓል፡፡
ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ በተለያዩ ፈፃሚ አካላት በዕቅድ የተያዙ የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥራዎች በታቀደላቸው የማስፈፀሚያ ጊዜና ሰብአዊ ሀብት እንዲከናወኑ በየደረጃው ለሚገኙ ፈፃሚ አካላት የበጀት ድጋፍ ከማድረግ አልፎም የመፈፀም አቅማቸውን ለማሣደግ የሚረዳ ድጋፋዊ ክትትል አድርጓል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ሥልጠናዎችና የልምድ ልዉዉጥ እድሎች በየደረጃው ለሚገኙ የማስ/ጽ/ቤት ባለሙያዎችና ለተለያዩ አካላት ተሰጥቷዋል፡፡

በ2000 በጀት አመት ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ 113 የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 3 ሁለተኛ ድግሪ & 342 ዲፕሎማና 45 ሠራተኞች ደግሞ 12ኛ ክፍልና ከዚያ በታች በድምሩ 503 ሠራተኞችን ይዞ በዕቅድ የተያዙ ሥራዎችን እያስተባበሪ በማስፈፀም ላይ ይገኛል፡፡ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያለዉን የሰዉ ሃይል በአግባቡ በመጠቀም የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የ3ተኛዉን ምዕራፍ የሚሊኒም ፀረ ኤድስ ዘመቻ በዋና ስልትነት በመጠቀም ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ አመርቂ ዉጤት ተመዝግቧል፡፡
የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ የሰው ኃይልና ተቋማት አቅም ግንባታ ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን በበጀት አመቱ በየደረጃው በርካታ ስልጠናዎች ለፈፃሚ አካላትና ለማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ተሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ተሞክሮዎችንና የተሻሉ አሰራሮችን ለመቅሰም ወደ ዩጋንዳ የስራ ጉብኝት በሦስት ዙር ተደርጓል፡፡

በ2000 በጀት ዓመት በየደረጃው በዕቅድ በመመራት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በስፋት የተጀመረበትና የሦስተኛው ምዕራፍ የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻ በየደረጃዉ ለሚገኙ አስፈፃሚ የአመራር አካላት ሥራዎች ተቆጥረዉ የተሰጡበት በመሆኑ አበረታች ክንውን የተመዘገበበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመስክ ጉብኝት የተገኘዉ መረጃ አበረታች አፈጻጸም መመዝገቡን ያስረዳል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከተሰሩት የአቅም ግንባታ ሥራ ዉስጥ የተለያዩ መመሪያዎች በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው ከክልል እስከ ወረዳ ለሚመለከታቸው አካላት የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ከፍተኛ የመፈጸም አቅም ሊፈጥሩ የሚችሉ መመሪዎችም ተዘጋጅተው ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን እነሱም፤

- የፕሮጀክት ምዘና መመሪያ፣
- የፋይናንስ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ
- የክትትልና ግምገማ መመሪያ፣
- የፕሮጀክት አስተዳደር መመሪያና
- የዕቃ ግዢ መመሪያዎች ናቸው፡፡

የክልሉ ህብረተሰብ በአዲሱ ሚሊኒየም የኤች አይ ቪ/ኤድስን ስርጭት ለመግታት በሚደረገው ጥረት የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት ተጠናክረው ተሰጥተዋል፡፡ የተጠናከረ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህብረተሰቡ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ በባለቤትነትና ግንባር ቀደም ተዋናይነት እንዲሰለፍ እየተደረገ ነው፡፡

የክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት የተለያዩ ፈፃሚ አካላት ቀጣይነት ባለዉ መልኩ የፀረ ኤድስ ሥራዎችን ከማስተባበሩና ሃብት ከማሰባሰቡ በተጨማሪም የሚካሄዱ ተግባራትን አፈፃፀም በየደረጃው በመከታተልና የቴክኒክ እገዛ በመስጠት በእቅድ የተያዙ ጉዳዮች በተቀመጠላቸዉ የጊዜ ገደብና የማስፈጸሚያ ሀብት እንዲከናወኑ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የ2000 በጀት አመት እቅድ አፈጻጸም የተለያዩ ጉዳዩችን አካትቶ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 2. ዋና ዋና የተግባራት አፈፃፀም

## 2.1. መከላከል

በ2000 በጀት ዓመት በዕቅድ ተይዘው በተለያዩ አካላት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የቫይረሱን ስርጭት የመከላከል ሥራ አንዱና ዋነኛዉ ነው:: ባለፈዉ የበጀት አመት የተጀመረው የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻም ህብረተሰቡን በስፋት በመቀስቀስ ግንዛቤ እንዲያገኝ በማድረግ የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት፣ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል፣ የፀረ- ኤች አይ ቪ መድሃኒት ለሚያስፈልጋቸዉ ሰዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣የህክምና ባህሉን በማሳደግ በተለይም ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ የአባለዘር በሽታዎችን ፈጥኖ እንዲታከሙ በማድረግና እንዲሁም በኮንዶም አጠቃቀም...ወዘተ በርካታ ውጤቶች ተገኝተዋል::

### *2.1.1. የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት*

ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለበሽታው ምንነት፣ መተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎች እንዲሁም ስለሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና ለሕብረተሰቡ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት በየጊዜዉ በተለያዩ መንገዶች እየተሰጠ ይገኛል::

በ2000 በጀት አመት በዕቅድ ከተያዘዉ 14,000,000 ዉስጥ ለ16,580,710 ሕዝብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በተለያዩ ስልቶች ተሠጥቷል:: በዕቅድ የተያዘው 118.43 % ተከናውኗል:: አፈፃፀሙ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 2,392,695(17%) ብልጫ አሳይቷል:: ለዚህ ከፍተኛ አፈፃፀም ዋነኛ ምክንያት የሆኑት በ2ኛውና በ3ኛው ምዕራፍ በተከታታይ እየተካሄዱ ያሉት የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻዎች ናቸው:: በዘመቻው ከፍተኛ ትኩረት ከተደረገባቸዉ አበይት ተግባራት መካከል የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ& ቫይረ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል ፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና አገልግሎቶች ተጠቃሚዎችን ማሳደግ እና የማህበረሰብ ዉይይትና ሌሎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ተግባራት በዋናነት ይገኙበታል:: የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቱ

- በገጽ ለገጽ ገለፃ ዝግጅቶች
- በሚነበቡ የመረጃና የትምህርትቁሳቁሶች
- ከሚዲያ በሚደመጡ መረጃዎች
- በስነ ጽሑፍ በድራማና በግጥም

- በሙዚቃ ዝግጅቶች
- በአቻ ለአቻ ውይይት
- በሚኒሚድያ በሚደረግ ቅስቀሳ
- በማህበረሰብ ውይይት
- በፓናል ውይይት
- ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ ያለባቸው ሰዎች በሚሰጡት የምስክርነት ቃል

...ወዘተ የሚሉት በግንባር ቀደምትነት ይገኙበታል። በእምነት ተቋማትና በዓላት በት/ቤት በገበያና በስብሰባ ቦታዎች ላይ ግንዛቤው እንዲፈጠር ጥረት ተደርጓል። በተለይ የ2000 ዓ.ም. የዓለም ኤድስ ቀን በብሔራዊ ደረጃ በክልላችን እንዲከበር በመወሰኑ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ንቅናቄና አመራሩን የሚያሳትፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዓሉ በደብረ ብርሃን ከተማ እጅግ ደማቅ በሆነ ሁኔታ የተከበረ ሲሆን በየደረጃውም ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ መከበሩ እየተካሄደ ላለው የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻ ስኬት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በክልሉ ሁሉም ቀበሌዎች የሕዝብ ንቅናቄ መድረኮች የተካሄዱ ሲሆን በየደረጃው ያለው የአመራር ሚናም ከመቸውም በላይ ጎልቶ እየታየ መሆኑ በመስክ ክትትል ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በህዝባዊ በዓላትና የስፖርት ዉድድሮች ወቅት የተመረጡ ወቅታዊ መልዕክቶች እንዲተላለፉ ተደርጓል። በአጠቃለይ በክልል ደረጃ በእቅድ ተይዘው የተከናወኑት ተግባራት ከዚህ እንደሚከተለዉ ቀረቧል ።

የ 2000 በጀት አመት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ዕቅድ አፈጻጸም በዞን ደረጃ

| ተ.ቁ | ዞን/ወረዳ | መለኪያ | የ2000 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር% |
| 1 | ደ/ወሎ | ቁጥር | 1956049 | 1409318 | 72.05 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | » | 1000000 | 1767715 | 176.77 |
| 3 | ምስ/ጎጃም | » | 1484415 | 2069829 | 139.44 |
| 4 | አዊ | » | 844584 | 1408026 | 166.71 |
| 5 | ምዕ/ጎጃም | » | 3061617 | 3427021 | 111.94 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | » | 2111460 | 2409619 | 114.12 |
| 7 | ደ/ጎንደር | » | 1504635 | 1740703 | 115.69 |
| 8 | ሰ/ወሎ | » | 1126112 | 1108539 | 98.44 |
| 9 | ዋግ ኸምራ | » | 264378 | 501887 | 189.84 |
| 10 | ኦሮሚያ | » | 288594 | 288967 | 100.13 |
| 11 | ባህር ዳር | » | 358156 | 449086 | 125.39 |
| | ድምር | | 14,000,000 | 16,580,710 | 118.43 |

## *2.1.2. መረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁስ*

በተለያዩ የመረጃና ትምህርት ቁሳቁስ አማካኝነት ለሕብረተሰቡ ትምህርት መስጠት የባሕሪ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል የድጋፍ እንክብካቤ እንዲሁም የህክምና አገልግሎት ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ይህ ዘርፍ ቁልፍ ሚና አለው፡፡

ይሁን እንጅ በተለያዩ አካላት ተዘጋጅተው ለሕብረተሰቡ የሚሠራጩት የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁሶች የሕብረተሰቡን የግንዛቤ ደረጃ ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት 2000 የበጀት አመት ውስጥ ከተሰራጩት የመረጃና ትምህርት ቁሳቁሶች መካከል በራሪ ጹሑፎች& ብሮሸሮች ፣ ፖስተሮች &መጽሔቶችና ሌሎች የህትመት ዉጤቶች በግንባር ቀደምትነት ይገኙበታል፡፡ በጥቅሉ በበጀት አመቱ 290000 ህተመቶች ለማሰራጨት ታቅዶ በክልል ደረጃ 74,516 በዞኖች ደረጃ ደግሞ 1,210,047 በድምሩ 1,299, 079 የተለያዩ የመረጃ ፣ ትምህርትና ቁሳቁስ ስርጭት ተካሂዷል፡፡ ይህም የዕቅዱ 447.95% ለማሰረጨት የተቻለ ሲሆን

አፈጻጸሙ ከተያዘዉ እቅድ በላይ 347.95% መፈጸሙን መረጃዉ ይጠቁማል። አፈፃፀሙ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 41% ብልጫ አለዉ ።

በመረጃ ማዕከሉ 175 የቪዲዮና የሲዲ መረጃዎች በትውስት ለተጠቃሚዎች ተሰጥቶአል። በ2000 በጀት አመት 6689 ገፅ መረጃዎች በማባዛት ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል።በመረጃ ማዕከሉ 13699 ሠዎችን በኢንተርኔት፤በቪዲዮና የንባብ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል 459 ሴቶች ናቸዉ ።
በተመሳሳይ መልኩ በ4ኛዉ ሩብ አመት በጎንደርና በደሴ ከተማ የመረጃ ማዕከሎች ተከፍተዉ ለሕብረተሰቡ አገልገሎት መስጠት የጀመሩ ሲሆን ማዕከላቱን ለማቋቋም በብር 2.2 ሚሊዮን በላይ የገንዘብ ወጪ ተደርጋል ።

## 2.1.3. የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት

የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ከሚሰጣቸዉ ጥቅሞች ጥቂቶቹ:-

- ✓ የቫይረሱን ሥርጭት ባለበት ለመግታት
- ✓ ከቫይረሱ ነፃ የሆኑ ልጆች እንዲወለዱ ለማድረግ
- ✓ ጤነኛ ቤተሰብ ለመመስረት
- ✓ የወደ ፊት ሕይወትን በዕቅድ ለመምራት
- ✓ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ለመጠቀም
- ✓ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም በኤች አይ ቪ/ኤድስ ምክንያት ለሚከሰቱ ተጓዳኝ በሽታዎች ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ለማድረግ መግቢያ በር ነው።

በአሁኑ ወቅት በክልሉ 175 የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ደግሞ 30 በድምሩ 205 የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ በሚሊኒየሙ የፀረ ኤድስ ዘመቻ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ቅስቀሳ እየተደረገ ከመሆኑም በላይ በክልሉ የማህበረሰብ ውይይት እየተካሄደ በመሆኑና ከፍተኛ የሆነ የመመርመር ፍላጎት በመፈጠሩ ከመደበኛ የአገልግሎት መስጫዎች በተጨማሪ በ560 በላይ በተንቀሳቃሽ ጣቢያዎችም አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ከጤና ጥበቃ ቢሮና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር እያደረገ ባለው የዘመቻ ሥራ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎቱ በነፃ /ያለ ክፍያ/መካሄዱም በተጠቃሚው ህብረተሰብ በኩል ከፍተኛ ፍላጐት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ አድርጎአል።

በ2000 የበጀት አመቱ ለ800,000 ሰዎች የኤች አይ ቪ የምክርና ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ1,403,241 ሰዎች አገልግሎቱ ተሰጥቷል፡፡ ይሄም ከዕቅዱ 175% አፈፃፀም ያለዉ ሲሆን ከ1999 ዓ.ም ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ1,027,153 ሰዎችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በማድርግ ከፍተኛ ብልጫ አሳይቷል፡፡ ይህ ውጤት የመጣው የማህበረሰብ ውይይቱ በሰፋት መስፋፋቱ ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ግንዛ በሰ በተለይ የሴቶች መመርመር ከፍተኛ እንዲሆን በማድረዛቤ መስጠቱና የሚሊኔም የፀረ-ኤድስ ዘመቻ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል በኩል የሴቶች ጉዳይ ቢሮ የአማራ ክልል የፀረ-ኤድስ የሴቶች ጥምረት ንቅናቄና ሴቶች ማህበር ለውጤቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በበጀት አመቱ ከተመረመሩት ከ792,050 ወንዶች ውስጥ 21,449 እንዲሁም ከተመረመሩት 611,191 ሴቶች ውስጥ 29,8437 ቱ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ተገኝቶባቸዋል፡፡ በሪፖርቱ በበጀት አመቱ ከተመረመሩት ውስጥ በቁጥር ወንዶቹ የሚበልጥ ቢሆንም በብዛት ኤች አይ ቪ በደማቸው የተገኘባቸው ሴቶች መሆናቸዉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በመከላከሉና በድጋፍ አሰጣጡ እንዲሁም በህክምናው በኩል ለሴቶች የተለየ ትኩረት መስጠት ይገባል ፡፡

በአጠቃላይ በክልሉ የኤች አይ ቪ ስርጭትን ለመግታት የሚያስችሉ የባህሪ ለዉጥ አመላካቾች አሉ ፡፡ ዋና ዋናዎቹም፡-

- ✓ የደም ምርመራ በህ/ሰቡ እየተለመደ መሆኑን፣
- ✓ ህብረተሰቡም ከኤች አይ ቪ ተጋላጭነት ራሱን የመጠበቅ ልምዱ መሻሻሉን
- ✓ የኮንደም የመጠቀም ፍላጎት እወቀትና ክህሎት እየጨመረ መምጣቱ
- ✓ የህብረተሰቡ ተሳትፎ መጨመሩ
- ✓ ማግለልና መድሎ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱ
- ✓ በህብረተሰቡ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች መወገዝ መጀመራቸዉ
- ✓ ወ.ዘ.ተ ሊጠቀሱ የሚችሉ የባህሪ ለዉጥ አመልካቾች መለኪያዎች ናቸዉ ፡፡

# የ2000 በጀት አመት  የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት እቅድ አፈጻጸም በዞን ደረጃ

| ዞን /ወረዳ | መ/ ያ | አመቱ ዕቅድ | የአመቱ ክንዉን | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት ያደረጉ | | | የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ያደረጉ | | | ቫይረሱ የተገኘባቸዉ | | | ለድጋፍና ክብካቤ ሪፈር የተፃፈላቸው | | | % |
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወ | ሴ | ድምር | |
| ደ/ወሎ | ቁጥር | 69501 | 140106 | 128985 | 269091 | 144281 | 131371 | 275652 | 4273 | 6599 | 10872 | 2188 | 3207 | 5395 | 375 |
| ሰ/ሸዋ | » | 172362 | 124316 | 81560 | 205876 | 124303 | 81530 | 205833 | 1885 | 2586 | 4471 | 118 | 175 | 293 | 119 |
| ምስ/ጎጃም | » | 71984 | 105279 | 68949 | 174228 | 105279 | 68949 | 174228 | 2341 | 3111 | 5452 | 2341 | 3111 | 5452 | 242 |
| አዊ | » | 82445 | 53018 | 38966 | 91984 | 52961 | 38954 | 91915 | 728 | 1183 | 1911 | 97 | 173 | 270 | 111 |
| ምዕ/ጎጃም | » | 76791 | 68099 | 47318 | 115417 | 68099 | 47318 | 115417 | 1192 | 1782 | 2974 | -- | -- | -- | 150 |
| ሰ/ጎንደር | » | 41701 | 90971 | 80055 | 171026 | 90971 | 80055 | 171026 | 3834 | 4953 | 8787 | -- | -- | -- | 410 |
| ደ/ጎንደር | » | 122071 | 98588 | 68733 | 167321 | 98588 | 68733 | 167321 | 1454 | 2157 | 3611 | -- | -- | -- | 137 |
| ሰ/ወሎ | » | 60049 | 45970 | 43759 | 89729 | 43896 | 41683 | 85579 | 1998 | 2681 | 4679 | 323 | 473 | 796 | 143 |
| ዋግ ኽምራ | » | 14638 | 13939 | 13371 | 27310 | 16168 | 10909 | 27077 | 361 | 339 | 700 | 30 | 33 | 63 | 185 |
| ኦሮሚያ | » | 53707 | 35279 | 32770 | 68049 | 23469 | 19983 | 43452 | 550 | 699 | 1249 | 160 | 188 | 348 | 81 |
| ባህ/ዳር | » | 34751 | 24052 | 21713 | 45765 | 24035 | 21706 | 45741 | 2833 | 3347 | 6180 | 1136 | 1336 | 2472 | 132 |
| ድምር | | 800,000 | 799617 | 626179 | 1425796 | 790,050 | 611,191 | 1,403,241 | 21449 | 29437 | 50886 | 6393 | 8696 | 15089 | 174 |

## *2.1.4. ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል*

የኤች አይ ቪ/ኤድስን ሥርጭት ለመግታት ከፍተኛ ትኩረት ከተሠጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ ከእናት ወደ ልጅ ቫይረሱ እንዳይተላለፍ መከላከል ነው፡፡ ቫይረሡ በደማቸው የተገኘባቸው ነፍሰጡር እናቶች ቫይረሱ ወደ ህፃኑ እንዳይተላለፍ የሚያስችለውን ሕክምና እንዲያገኙ ግንዛቤ በመስጠትም ሆነ አገልግሎቱን በማቅረብ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜም እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

በ2000 በጀት አመት ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ በ168 የጤና ድርጅቶች አገልግሎቱን የማቅረብ ስራ እየተሰራ ሲሆን ለ30,000 እናቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 46,234 እናቶች አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡ የእቅዱ 154.11% ተግባራዊ ሆኗል' ከአለፈዉ አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 24,244 (110%) ብልጫ አሳይቷል' በ2000 በጀት አመት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል 1997 እናቶች ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ተገኝቶባቸዋል፡፡ 1205 እናቶችና 728 ሕጻናት ኔቨራፒን እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡ በትዳር አጋሮች ወይም ጓደኞች ዙሪያ የጎላ ባይባልም በመጠኑም ቢሆን በተፈጠረዉ የባህሪ ለዉጥ የተነሳ 8083 ወንድ የትዳር አጋሮች የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ አድርገዋል ከነዚህ ውስጥ 221 ወንዶች ቫይረሱ መደማቸው ውስጥ ተገኝቶባቸዋል፡፡

ይሁን እንጅ በዚህ ዘርፍ የተደረገዉን እንቅስቃሴን ተከትሎ የመጣዉ ለውጥና የተመዘገበዉ ዉጤት በጣም አነስተኛ ነዉ፡፡በወንድ የትዳር አጋሮች ዙሪያ ስፋት ያለዉ እንቀስቃሴ ከተደረገ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚደረገዉ እንቅስቃሴ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ይቻላል ተብሎ ይገመታል ፡፡

ስለዚህ በቀጣዩ በ2001 በጀት አመት ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት በየደረጃዉ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በስፋት መንቀሳቀስና አመርቂ ዉጤት እንዲመዘገብ ጥረት ሊደረግ ይገበዋል፡፡

# የ2000 የበጀት አመት ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል እቅድ አፈጻጸም በዞን ደረጃ

| ተቁ | ዞን /ወረዳ | መለኪያ | አመታዊ ዕሓጸ | አመቱ ክንዉን | | | | | | የትዳር አጋሮች የተመረመሩ | | ምርመራ ያደረጉ ዕቅድ ክንዉን % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ቅድመ የምክር አገልግሎት ምርመራ ያደረጉ | የኤች አይቪ ምርመራ ያደረጉ | ቫይረሱ የተገኘባቸዉ | ድህረ ምርመራ የምክር አገልግሎት ያገኙ | NVP የወሰዱ እናቶች | NVP የወሰዱ ህፃናት | የተመረመሩ | ቫይረሱ የተገኘባቸው | |
| 1 | ደ/ወሎ | ቁጥር | 3792 | 9066 | 7611 | 360 | 6840 | 165 | 129 | 441 | 68 | 200.71 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | " | 4006 | 6562 | 5350 | 168 | 4856 | 79 | 71 | 571 | 27 | 133.55 |
| 3 | ምስ/ጎጃም | " | 3381 | 8789 | 5567 | 273 | 4354 | 195 | 79 | 1190 | 35 | 164.66 |
| 4 | አዊ | " | 3020 | 3644 | 3016 | 96 | 2178 | 51 | 38 | 727 | 16 | 99.87 |
| 5 | ምዕ/ጎጃም | " | 2245 | 6107 | 4886 | 120 | 4313 | 67 | 52 | 1355 | 22 | 217.64 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | " | 4019 | 19961 | 8975 | 384 | 7977 | 335 | 222 | 1251 | 1 | 223.31 |
| 7 | ደ/ጎንደር | " | 3193 | 5571 | 4520 | 161 | 4520 | 51 | 37 | 2014 | 31 | 141.56 |
| 8 | ሰ/ወሎ | " | 2663 | 3565 | 2474 | 172 | 2682 | 81 | 23 | 393 | 15 | 92.90 |
| 9 | ዋገ ኽምራ | " | 1459 | 258 | 514 | 5 | 106 | 4 | 5 | 7 | 4 | 35.23 |
| 10 | ኦሮሚያ | " | 1992 | 2932 | 1642 | 62 | 1376 | 39 | 33 | 70 | 2 | 82.43 |
| 11 | ባህር ዳር | " | 230 | 1804 | 1679 | 196 | 1760 | 138 | 39 | 64 | --- | 730.00 |
| | ድምር | | 30,000 | 68,259 | 46,234 | 1997 | 40,962 | 1205 | 728 | 8083 | 221 | 154.11 |

## 2.1.5. የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ አፈጻጸም

የበጀት አመቱ የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ የአለፈዉን አመት ሁለት ዘመቻዎች መሰረት በማድረግ ከመስከረም 1/2000 ጀምሮ በክልሉ የ3ኛ ምዕራፍ የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ በየደረጃዉ በስፋት እየተካሄደ ይገኛል::በዚህ ዘመቻም ከሚደረገዉ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ የተነሳ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤና እዉቀት በኤች አይ ቪ ዙሪያ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል ::በየደረጃዉ በስፋት ህብረተሰቡ የሚሳተፍበት በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የባህሪ ለዉጥ ይፈጠራል ተብሎ ተገምቷል፡፡

በክልሉ ከመስከረም ወር 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እየተካሄደ ባለው 3ኛው ምዕራፍ የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ ሁሉንም አካላት ያሳተፈ ዕቅድ ታቅዶ በየደረጃው ላለው አመራር በማስተላለፍ ወደተግባር ተገብቷል፡፡

የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ የ10 ወር እቅድ አፈጻጸም እንደሚያመለክተዉ ብቻ 1,330,617 ሰዎች በምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ተሰጧል፡፡ 42,592 እናቶች ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል እንዲሁም ከ21000 ሰዎች በላይ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሐኒት ህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ የተገኘዉ ውጤት አመርቂ በመሆኑ በቀጣይም በየደረጃዉ እየተደረጉ ያሉት እንቅስቃሴዎች በበለጠ ተጠናክረዉ እንዲቀጥሉና እስከ ጳጉሜን 5/2000 ዓ.ም ድረስ በሁሉም ተግበራት የተጣለዉ ግብ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጸም በተለይ የክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ እረፍት የለሽ ዘረፈ ብዙ እንቅስቀሴ ሊያደረጉ ይገበል፡፡ በእቅድ በመመራት እየተከናወነ ያለው ተግባር የላቀ ዉጤት የሚመዘገብበት የሁሉንም ሴክተሮች ተቀናጅቶ በመሥራት ውጤቱን ዘላቂ ማድረግ ነው'

የሚሊኒየም 3ተኛዉ ምዕራፍ የፀረ ኤድስ ዘመቻ በቀጣዩም የበጀት አመት የላቀ ውጤት እንዲመዘገብበት የሚከተሉትን አብይት ተግባራት በግባትነት መጠቀም የግድ ይላል '

- ✓ ለዘመቻዉ የሚያስፈልጉ ቁሳቀሶችን ቅድሚያ በተቋማት ደረጃ ማሟላት
- ✓ በጤና ተቋማቶች የሚገኙ ባለሞያዎች በከፍተኛ ሁኔታ መጠቀም
- ✓ የማህበረስብ ውይይትና ውሳኔዎቹን አጠናክሮ ማሰቀጠል
- ✓ የህዝብ ንቅናቄንና ተሳትፎ ማቀጣጠልና የአገልግሎቶቹ ተጠቃሚ ማደረግ
- ✓ የተለያዩ ፈጻሚና አጋር ድርጅቶችን (የመንግስት& መንግስታዊ ያልሆኑና ሌሎች ተቋማት) በሰፋት በየደረጃዉ ማንቀሳቀስ

- ✓ ለዘመቻዉ የተመደበዉ በጀት በአግበቡ መጠቀምና በወቅቱ በሥራ ላይ በማዋል ማወራረድ
- ✓ በየደረጃዉ የሚገኘዉን የአመራር አካለት በመጠቀም ህዝቡን ማንቀሳቀስና በቅርብ ለተዘጋጁለት አግልግሎቶች ተጠቃሚ ማድረግ
- ✓ ለክትትልና ግምገማ ሥራዎች ትኩረት መስጠትና በቂ በጀት መመደብ
    - ጠንከራና ዉጤታማ የመስክ ጉብኝት በየደረጃዉ በማካሄድ ለፈጻሚ አካላት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት
    - የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ስብሰባዎችን ማካሄድና የግምገማዉን ዉጤቶች መጠቀም
    - የመደበኛ ጉብኤዎችን በየ ደረጃዉ ማካሄድና የሚቀመጡ የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን በግባትነት መጠቀምና የላቀ ዉጤት ማስመዝገብ
- ✓ በዞኖችና በወረዳዎች መካከል ቀጣይነት ያለዉ የዉድድር መንፈስ የሚታገዝ ሥራ መፈጠር
- ✓ የመረጃ አያያዝና ልዉዉጥ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ በየደረጃዉ በተግበር ወዘተ የሚሉትን እስትራቴጅዎችን መጠቀም ለቀጣዩ አፈጻጸማችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## *2.1.6. የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት አገልግሎት*

ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ ግንኙነት ዋና የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገድ በመሆኑ ኮንዶምን በአግባቡና ሁልጊዜ ህብረተሰቡ ሊጠቀም የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ነው፡፡ የኮንደምን የመከላከል ብቃት ለህብረተሰቡ በማሳወቅ የክልሉ ህዝብ ለኮንደም ያለዉን እዉቀትና የመጠቀም ችሎታዉ እንዲያድግ ያላሳለሰ ጥረት ሊደረግ ይገበዋል ' የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ና ዲኬቲ ኢትዮጵያ ኮንዶምን በማስተዋወቅና በማሠራጨት በዋናነት የሚሰሩ አካላት ሲሆኑ በሌሎች አካላት ማለትም በቤተሰብ መምሪያ በአልማ በፀረ ኤድስ ክበባት በግል የጤና ድርጅቶች እንዲሁም በሱቆች እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በ2000 በጅት አመት በዞኖች ደረጃ ለተለያዩ አካላት ከዲኬቲና ጤና ጥበቃ ቢሮ የደረሳቸዉን **7,275,813** ኮንደም ለማሰራጨት ቸለዋል'

በአጠቃለይ 2000 የበጀት አመት በክልሉ 12,000,000 ኮንደሞችን ለማሰራጨት ታቅዶ በዲኬቲ 8,862,766 ኮንደሞች በክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ደግሞ 2,157,116 ኮንደሞችና

ከአይቴክ ኢትዮጵያ ከተገኘው 3000000 ውስጥ 1300000 ጥቅም ላይ እንዲውል ሲሆን በድምሩ 12,319,882 ወይም የእቅዱን 102.6 በመቶዉ ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 3,516,608 ኮንደም ብልጫ አሳይቷል፡፡ ይሄም የክልሉ ህብረተሰብ የኮንዶም ተጠቃሚነቱና ስለኮንዶም ያለው ግንዛቤ መጨመርና ከኤች አይ ቪ ተጋላጭነት ራሱን የመጠበቅ በጐ አዝማሚያ እንዳለው ያሳያል፡፡

## 2.1.7. የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና የህክምና አገልግሎት መስጠት

የአባላዘር በሽታዎች የኤች አይ ቪ/ኤድስን ስርጭት ከሚያባብሱት ከዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ ሲሆን በአባለዘር በሽታዎች የተያዙ ሠዎች ለቫይረሱ ያላቸው ተጋላጭነት ከጤነኛ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ተጋላጭ በመሆናቸው የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግና የተጋለጡትን ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በ2000 በጀት ዓመት ለ40000 ሰዎችን ህክምና ለመስጠት ታቅዶ ለ28,888 ሰዎች የአባለዘር በሽታ ሕክምና አገልግሎት ተሰጧል፡፡ ይሄም የዕቅዱ 72.2% ነው፡፡ የአባላዘር በሽታዎች ስርጭት መቀነስ የህብረተሰቡ የግንዛቤ ደረጃ እያደገ መሆኑን ለኤች አይ ቪ አጋላጭ ከሆኑ ተግባራት እየተቆጠበ መምጣቱን፣ የኮንዶም ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር፣ በወቅቱ ወደ ጤና ተቋማት ሄደው ህክምና ማግኘታቸው ለሌላው ህብረተሰብ እንዳይተላለፍ አስተዋጽኦ ማድረጉን ያመለክታል፡፡

| ተ.ቁ | ዞን | መለኪ. ያ | የ2000 በጀት አመት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንዉን | | | ንፅፅር % |
| | | | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ደ/ወሎ | ቁጥር | 5231 | 3043 | 3561 | 6604 | 102 |
| 2 | ሰ/ሸዋ | " | 4277 | 1057 | 983 | 2040 | 31 |
| 3 | ምስ/ጎጃም | " | 6555 | 2516 | 1238 | 3754 | 32 |
| 4 | አዊ | " | 1777 | 686 | 790 | 1476 | 54 |
| 5 | ምዕ/ጎጃም | " | 6506 | 665 | 628 | 1293 | 13 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | " | 6509 | 3600 | 3347 | 6947 | 69 |
| 7 | ደ/ጎንደር | " | 2195 | 978 | 941 | 1919 | 57 |
| 8 | ሰ/ወሎ | " | 1731 | 870 | 838 | 1708 | 64 |
| 9 | ዋግ ኸምራ | " | 3332 | 358 | 321 | 679 | 13 |
| 10 | ኦሮሚያ | " | 911 | 440 | 648 | 1088 | 78 |
| 11 | ባህር ዳር | " | 976 | 644 | 736 | 1380 | 92 |
| | ድምር | " | 40000 | 14857 | 14031 | 28888 | 72.2 |

## *2.1.8. የማህበረሰብ ውይይት*

ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት አንዱና ተጨባጭ ለውጥ እያመጣ ያለው የማህበረሰብ ውይይት ነው፡፡

የማህበረሰብ ውይይት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ በመወያየት ችግሩን በመለየት አካባቢያዊ መፍትሔ በማስቀመጥ በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በድጋፍና እንክብካቤ በአድልዎና መገለል ወዘተ ዙሪያ ጥልቅና ተከታታይ የሆነ ውይይት በማካሄድ አቅሙን እያጐለበተ ይገኛ ል፡፡

የማህበረሰብ ውይይት ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከል በመቆጣጠር ድጋፍና እንክብካቤ እንቅስቃሴ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሲሆን ለአብነትም፡-

- የተወያዮች ቁጥርና ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑ
- ተወያዮች ግንባር ቀደም የደም ምርመራ ተጠቃሚ መሆናቸው
- ተጨማሪ የውይይት ጣቢያዎች እንዲከፈቱ ጥያቄዎች መበራከቱ
- ከዚህ በፊት ለኤች አይ ቪ መስፋፋት ምክንያት የነበሩ በርካታ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መቀነሳቸዉ፣

- ህብረተሰቡ በድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት ጉልህ የሆነ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑ፣
- ህብረተሰቡን ያሳተፈ የፀረ ኤችአይቪ/ኤድስ ንቅናቄ እንዲፈጠር ማድረጉ ፣
- ህብረተሰቡ እያገኘ ባለው ግንዛቤ የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ በመከላከል እንዲሁም የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚነቱ እንዲጨምር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡
- የማህበረሰብ ውይይት አድልዎና መገለል በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪም የማህበረሰብ ውይይት ህብረተሰቡ ከጠባቂነት መንፈስ ተላቆ በልማት ስራ እንዲሳተፍ፣ በኤች አይ ቪ/ኤድስ የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች በገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሳተፉ አይነተኛ መፍትሄ እየሆነ ይገኛል፡፡ በነዚህና በሌሎች የማህበረሰብ ውይይት ጥቅሞች የተነሳ በክልሉ በሁሉም ቀበሌዎች እንዲጀመር ተደርጓል፡፡
- የማህበረሰብ ውይይት የሚካሄድባቸው ቀበሌዎች ብዛት **3309** የደረሰ ሲሆኑ ከዕቅዱ 96.6% ሲሆን የጣቢያዎችም ቁጥር **3422** ደርሶአል፡፡ከ1443 ነባር የማህበረሰብ ውይይት ጣቢያዎች በተጨማሪ 1979 አዲስ ጣቢያዎች በበጀት አመቱ ተከፍተዋል፡፡ በውይይቱም **254606** በላይ ተሳታፊዎች ይገኛሉ፡፡

በ2000 የበጀት አመት በዞን ደረጃ የሚገኙ የማህበረሰብ ዉይይት አሰልጣኞችና አመቻቾች ብዛት.

| ተቁ | ዞን | የአሰልጣኞች ብዛት | | | የአመቻቾች ብዛት | | | ስራ ያልጀመሩ አመቻቾች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | አሮሞ | 7 | 1 | 8 | 129 | 110 | 239 | 18 | 24 | 42 |
| 2 | ባህርዳር | 6 | 2 | 8 | 26 | 48 | 74 | 0 | 0 | 0 |
| 3 | አዊ | 20 | 3 | 23 | 23 | 361 | 384 | 0 | 0 | 0 |
| 4 | ምእ/ጎጃም | 18 | 4 | 22 | 239 | 681 | 920 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ምስ/ጎጃም | 24 | 3 | 27 | 583 | 780 | 1363 | 78 | 80 | 158 |
| 6 | ስ/ሸዋ | 30 | 7 | 37 | 415 | 685 | 110 | 38 | 73 | 111 |
| 7 | ደ/ወሎ | *22* | *2* | *24* | *97* | *451* | *548* | *0* | *203* | *203* |
| 8 | ስ/ወሎ | 21 | 13 | 34 | 120 | 452 | 572 | 9 | 59 | 68 |
| 9 | ደ/ጎንደር | 18 | 3 | 21 | 96 | 504 | 600 | 29 | 96 | 125 |
| 10 | ስ/ጎንደሮ | 24 | 7 | 31 | 299 | 952 | 1251 | 23 | 137 | 160 |
| 11 | ዋግህምራ | 4 | 0 | 4 | 17 | 241 | 258 | 0 | 4 | 4 |
| | ድምር | 194 | 45 | 239 | 2044 | 5265 | 6319 | 195 | 676 | 871 |

በ2000 የበጀት አመት የማህበረሰብ ዉይይት የሚካሄድባቸዉ ቀበሌዎችና በየጣቢያዎችና በመሳተፍ ላይ የሚገኘዉ ህዝብ ብዛት በዞን ደረጃ

| ተቁ | ዞን | የማህበረሰብ ውይይት | | በነባር ጣቢያዎች የተሳታፊዎች ብዛት | | | | በአዲስ ጣቢያዎች የተሳታፊዎችብዛት | | | | ጠቅላላ የተሳታፊ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቀበሌዎች ብዛት | ጣቢያዎች ብዛት | ነባር ጣበያ | ወ | ሴ | ድ | አዲስ ጣቢያ | ወ | ሴ | ድ | |
| 1 | አሮሞ | 112 | 114 | 46 | 2942 | 2098 | 5040 | 68 | 2675 | 2165 | 4840 | 9880 |
| 2 | ባህርዳር | 21 | 25 | 10 | 474 | 506 | 980 | 15 | 525 | 525 | 1050 | 2030 |
| 3 | አዊ | 194 | 202 | 89 | 2765 | 1721 | 5238 | 113 | 4258 | 2899 | 7157 | 12395 |
| 4 | ምእጎጃም | 392 | 397 | 111 | 4176 | 3050 | 7226 | 286 | 9587 | 9204 | 18791 | 26017 |
| 5 | ምስጎጃም | 426 | 504 | 220 | 8589 | 5636 | 14225 | 284 | 9897 | 7448 | 17345 | 31570 |
| 6 | ስ/ሸዋ | 412 | 418 | 138 | 8691 | 4928 | 13619 | 280 | 12477 | 7086 | 19563 | 33182 |
| 7 | ደ/ወሎ | 517 | 516 | 152 | 4691 | 5949 | 10640 | 364 | 11466 | 14014 | 25480 | 36120 |
| 8 | ስ/ወሎ | *309* | 316 | *172* | *6460* | *5188* | *11648* | *144* | *16323* | *15975* | *32298* | *43946* |
| 9 | ደ/ጎንደሮ | 300 | 306 | 117 | 3901 | 3226 | *7127* | 189 | 6098 | 5690 | 11788 | 18915 |
| 10 | ስ/ጎንደሮ | 501 | 497 | 329 | 12258 | 13083 | *25341* | 168 | 3100 | 2458 | 5678 | 26083 |
| 11 | ዋግህምራ | 125 | 127 | 59 | 2898 | 1874 | 4772 | 68 | 2760 | 2000 | 4760 | 9532 |
| ድምር | | 3309 | 3422 | 1443 | 57845 | 47259 | 105856 | 1979 | 79166 | 69464 | 148750 | 254606 |

በተመሳሳይ ደረጃ በአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ የሚደገፍ ከማህበረሰብ ውይይት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ህብረተሰቡን የሚያሳትፍ ፕሮግራም በመከናዎን ላይ የሚገኝ ሲሆን በክልሉ አራት ወረዳዎች (እስቴ፣አቸፈር፣ ዓንን እና ወንበርማ) 40 ቀበሌዎች በተጠናከረ ሁኔታ እየተካሄደ ይገኛል::

በዚህ ፕሮግራም ህብረተሰቡ እራሱን ከወረርሽኙ በመከላከል ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ለሌሎች አከባቢዎች አርዓያ ሊሆን የሚችል የባለቤትነትና የሃላፊነት ስሜት የሚፈጥር ስራ እየተሰራ ነው:: ዋና ዋና ተግባራትም ስልጠናዎች ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አሳታፊ የሆነ የምክክር ፕሮግራም የተሻሉ ስራዎች የልምድ ልውውጥ የሚካሄድበትና የመሳሰሉት ናቸዉ::

በዚህም መሠረት 312 የህብረተሰብ በጎ ፈቃደኞች ራሳቸው የደም ምርመራ በማድረግ ለህብረተሰቡ አርዓያ በመሆናቸው ህብረተሰቡ ተንቀሳቃሽ የደም ምርመራ አገልግሎት እየጠየቀ ይገኛል:: ጋብቻ በሚፈፀምበት ጊዜ ያለምርመራ እንዳይፈፀም በህብረተሰቡ ተወስኗል:: ህብረተሰቡ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ሠዎች ወላጅ ያጡ ህፃናትንና ጧሪ የሌላቸው አዛውንቶችን በመደገፍ ሃላፊነት እየወሰደ ይገኛል:: ለአብነትም ያህል በምስራቅ እስቴ

ወረዳ 70 ኩንታል እህል ተሰብስቦአል:: እድሮች በመደበኛ መዋጮች ላይ እስከ ሃምሳ ሳንቲም በመጨመር ድጋፍ እያድረጉ ነው:: ከዚህ ባሻገር ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመቀነስ ረገድም ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ሲሆን ለአብነትም ከአንድ በላይ ጓደኛ ያለው በህብረተሰቡ እንዲገለል በማድረግ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ እንዲቆም እንዲሁም ግርዛትና የመሳሰሉት እንዲቆሙ እየተደረገ ነው:: ሌላው ወረርሽኙን በመከላከል በመቆጣጠር ደጋፍና እንክብከቤ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የአመራር ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ዕድሮች መመሪያቸውን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ አንፃር እንዲቃኙ በማድረግና መገለልና መድልዎ እንዲቀንስ በማድረግ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛል'

## *2.1.9. ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት መስጠት*

በክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር  ለቫይረሱ ስርጭት በጣም ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችና አካባቢዎች ላይ አተኩሮ መሠራት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው::

በመሆኑም በክልሉ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች፣ ስርጭቱ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰባቸውን አካባቢዎች በመለየት ትክክለኛ ተግባራትንና ኘሮግራሞችን ለማካሄድ የሚያስችል ጥናት እየተካሄደ ይገኛል::

ጥናቱ በሲዲሲ ኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን እንደተጠናቀቀም ውጤቱ ለሚመለከታቸው የክልሉ አካላት ይቀርባል:: በቀጣይም በጥናቶች ግኝቶች ላይ ተመስርቶ በርካታ ሥራዎችን ለማካሄድ ታስቧል ::
በክልሉ የሴተኛ አዳሪነት የተስፋፋ በመሆኑ ሴቶችን ከዚህ ህይወት ለማውጣት የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ በገቢ ማስገኛና በህይወት ክህሎት ማሰልጠን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ 4000 ለሚደርሱ ሴተኛ አዳሪዎች በገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሰለጥኑ ታቅዶ በበጀት አመቱ 2823 ያህሉ በተለያዩ መልኩ ተደግፏል:: በዚህ ዘርፍ የተካናወነውን ሪፖርት ማድረግ ትልቅ ችግር እንዳለ ያሳያል::

በሌላም በኩል የፖሊስ አባላት፣ የመከላከያ ሠራዊትና ሚሊሻ፣ በማረሚ ቤቶች የሚገኙ የህግ ታራሚዎች ሹፌሮችና ሌሎች ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ መልኩ ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ ከሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶች ጋር በርካታ ተግባራትን ለማከናወን እንቅስቃሴ እየተደረገ  ይገኛል::

## ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለኤች አይ ቪ የተጋለጠ ቢሆንም ነገር ግን በስራ ባህሪያቸዉ በፆታና በዕድሜ የበለጠ ለቫይረሱ የተጋለጡ አካላት ላይ ትኩረት በማድረግ በአነስተኛ ወጭ ጊዜና የሰዉ ሃይል በፍጥነት የተሻለ ውጤት ማምጣት የሚቻል በመሆኑ የተለየ ጥረት እንዲደረግ ይጠበቃል። ከእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎችም ወጣቶች፣ ሴቶች፣ መለዮ ለባሹ፣ ተንቀሳቃሽ ሠራተኞች ይገኙበታል።በተገለፁት ተግባራት ተጠቃሎ የቀረበ ቢሆንም ለብቻው ጎላ ብሎ እንዲወጣ ለማድረግ በዚህ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ለመግለፅ ተሞክሯል።

- ወጣቱን ትኩረት ያደረጉ በፀረ ኤድስ ክበባት አማካኝነት በድራማ በስነ ጽሑፍ በሙዚቃ በመነባነብና በመሳሰሉት በመከላከሉ ዙሪያ በክልሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል።
- በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ላሉ የፀረ ኤድስ ክበባትንና የመረጃ ማዕከላትን ሚኒሚዲያዎችን በማቋቋምና በማጠናከር ወጣቱን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዲከላከል እየተደረገ ነው።
- በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከላከል ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በተለይም በሴተኛ አዳሪዎች ላይ ከተሰሩ ስራዎች በባህርዳር ከተማ ለ69 ሁለገብ የመከላከል ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል።
- በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የባህርይ ለውጥ እያመጣ ያለው የማህበረሰብ ውይይት ላይም ሴቶች ቢያንስ 50 በመቶ እንዲሆኑ ተደርጓል።
- በግሎባል ፈንድ ለ266 የሴተኛ አዳሪዎች የአቻ ለአቻ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል።
- ተጋላጭነትን በመቀነስ በግሎባል ፈንድ ድጋፍ ሴቶችና ሴተኛ አዳሪዎች ለ1060 ድጋፍ ተደርጓል።
- በብር ሸለቆ ማስልጠኛ ዉስጥ ለሚሰለጥኑ 4000 ምልምል ፖሊሶች መሰረታዊ የኤች አይቪ ኤድስ ትምህርት ተሰጥቷል ።

## 2.2. ድጋፍና ክብካቤ

ድጋፍና እንክብካቤ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ይሰጠዋል። ስለሆነም በክልላችን ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝና ለኤድስ ህሙማን እንዲሁም ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች በበርካታ ፈፃሚ አካላትና ማህበራት በኩል ድጋፍና ክብካቤ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል።በ2000 የበጀት ዓመትም በዚህ ዙሪያ በርካታ ተግባራት ተከናዉነዋል። በ2000 የበጀት አመት በክልሉ በጥቅሉ ለ113,000 ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸዉ ወገኖችና ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለመሰጠት ታቅዶ ለ 134„117 ሰዎች አገልገሎቱ የተሰጣቸዉ ሲሆን አፈጻጸሙም 119 በመቶ

ነዉ ። አፈጻጸሙ ከአለፈዉ አመት ጋር ሲነጻጸር 73015(119%) ብልጫ ያለዉ ሲሆን ይህም በበጀት አመቱ ለድጋፍና እንክብካቤ ዘርፍ በክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ከብር 35 ሚሊዮን በላይ ተመድቦ በተለያዩ አካላት ልዩ ልዩ ሥራዎች መከናወናቸዉ ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱን ይጠቁማል ።

## *2.2.1. ቫይረሱ በደማቸው ዉስጥ የሚገኝባቸውና የኤድስ ህሙማን ድጋፍና የማህበራት እንቅስቃሴ*

በ2000 የበጀት ዓመት ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝና ለኤድስ ህሙማን ከሴክሬታሪያት ጽ/ቤትና በሌሎች አጋር ድርጅቶች ድጋፍ 26,314 ያህሉ የመሠረታዊ ፍላጎቶች ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን ከታቀደው 45300 ውስጥ ክንውኑ 58% ይሆናል፡፡

በሴክሬታሪያት ጽ/ቤት በኩል የሚደረገው ድጋፍ በአብዛኛው በየማህበራት በኩል ተፈፃሚ እየሆነ የሚገኝ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎንም የማህበራቱን አቅም የማጎልበት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በአሁን ወቅት በድምሩ 134 የሚሆኑ ማህበራት ተደራጅተው አባሎቻቸው በተለያዩ የገቢ ማስገኛ የድጋፍና ክብካቤ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልም የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር እንዲሁም በሌሎች ተግባራት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤትም ለነዚህ ማህበራት የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ እንዲሁም የማህበራትን አቅም ለመገንባት ብር 13,853,922.4 ድጋፍ ተደርጓል፡፡
ማህበራቱ እያከናወኗቸው ያሉት የገቢ ማስገኛ ተግባራትም በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህልም፡፡

<u>በግብርና ልማት፡-</u> የእርሻ መሬት ከየአካባቢያቸው አስተዳደሮች በማግኘት የተለያዩ አዝርዕትን በማልማት ለገበያ ማቅረብ፣ ከብት ማድለብ፣ የወተት ልማት፣ በግና ፍየል እርባታ፣ የዶሮ እርባታ፣ ወዘተ... እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

<u>በንግድ ተግባራት</u>፡- የሸቀጣሸቀጥ ንግድ፣ የጽህፈት መሳሪያዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የእህል ወፍጮ፣ የእንጨት ስራ፣ የዳቦ መጋገር፣ ወዘተ... ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡
በየዞኖቹ በእነዚህ ተግባራት የተሻለ ስራ ሰርተው ለሌሎችም ልምድ በማካፈል ላይ የሚገኙ በርካታ ማህበራት የሚገኙ ሲሆን ለአብነትም

- በሰሜን ጎንደር ዞን በዳባት ወረዳ የሚገኘውም የብርሃን ተስፋ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ማህበር በ22 ሄክታር መሬት የባቄላ፣ የተልባ፣ የጤፍ፣ የስንዴ፣ የአብሽ እና የገብስ ምርት በማምረት ለገበያ አቅርበዋል፡፡
- በሰሜን ጎንደር ዞን በወገራ ወረዳ ተስፋ በር ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ማህበር 161 አባላት ያሉት ሲሆን ከወረዳ አስተዳደሩ በተሰጣቸው መሬት ላይ የቢራ ገብስ በማምረት ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡
- በሰሜን ጎንድር በምዕ/በለሳ ወረዳ የተሰፋ ሕይወት ማህበርም በተለያዩ የገቢማሰገኛ ሥራዎች (በከብት ማድለብ ፣፣በወፍጮ ፣ በእርሻ ሥራ ፣ በሱቅና በሻዉር አቅርቦት ወዘተ ) በመሰማራት በአጭር ጊዜ ዉስጥ ተጨባጭ ለዉጥ ያመጣ ማህበር ነዉ።
- በደቡብ ወሎ ዞን በኮምበልቻ ከተማ ተሰፋ ህይውት ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ማህብር በብሎኬት ማምረትና ሽያጭ ሥራ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየደረገተ ይግኛል ማህበሩ ቼንትሮ አዩቲ ፔር ኢትዮጵያ ባገኘዉ የገንዘብ ድጋፍ ገልባጭ የጭነት መኪና በመግዛት በገቢ ማስገኛ ሥራ ተሰማርቷል ።
- በምስ/ጎጃም ባሶሊበን የሚገኘው አዲስ ራዕይ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ማህበራት በተለያዩ የጥቃቅንና አነስተኛ ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ
- በምዕ/ጎጃም ዞን በይልማናዴንሳ ወረዳ ፋና ቫይረሱ በደማቸዉ ዉስጥ የሚገኙ ሰዎች ማህበራት በእርሻ በከብት እርነባታና በንግድ ሥራ ዘርፍ በገቢ ማሰገኛ ሥራዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ ፡፡
- በሌሎች ዞኖችም ማህበራቱ የከብት ማድለብ፣ የዛፍ ተከላ፣ የወፍጪ ቤት፣ የሸቀጣሸቀጥ ንግድ፣ የእርሻ ስራ፣ ወዘተ በማከናወን አምራች ዜጎች እየሆኑ ያሉ ሲሆን በየአካባቢው የሚገኘው የአመራር አካልም ከፍተኛ እገዛ እያደረገላቸው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡ ለማህበራቱ አባላት በጉልበትና በሞራል ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ማግለልና መድልኦን እያስቀረ ይገኛል፡፡
- የማህበራቱ አባላት እየተካሄደ ባለው የፀረ-ኤድስ ዘመቻ በህብረተሰብ ንቅናቄ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ የሚገኙ ሲሆን የቤት ለቤት እንክብካቤ በመሰልጠን ታመው አልጋ ላይ ለዋሉ ወገኖች ድጋፍና ክብካቤ ተግባራትም እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

**በ2000 በጀት ዓመት ቫይረሱ በደማቸው ለተገኘባቸው ወገኖች የተደረገ መሠረታዊ ፍላጎት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት የተጠቃሚዎች ብዛት**

| ተቁ | ዞን | መለኪያ | የአመቱ እቅድ | ክንውን (የተጠቃሚች ብዛትበፆታ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወንድ | ሴት | ድምር | ክንውን % |
| 1 | ባ/ዳር | ቁጥር | 14290 | 2377 | 5555 | 7930 | 55.5 |
| 2 | ምዕ/ጐጃም | " | 2436 | - | - | 1583 | 65 |
| 3 | ምስ/ጐጃም | " | 4123 | 940 | 1667 | 2597 | 62.9 |
| 4 | ሰ/ጎንደር | " | 3604 | 948 | 1266 | 2214 | 61.4 |
| 5 | ደ/ጎንደር | " | 2433 | - | - | 1414 | 104.7 |
| 6 | አዊ | " | 1442 | 170 | 398 | 568 | 58 |
| 7 | ዋግኽምራ | " | 1004 | 51 | 143 | 194 | 19.3 |
| 8 | ሰ/ወሎ | " | 1303 | - | - | 1610 | 123.6 |
| 9 | ደ/ወሎ | " | 9689 | 1271 | 4444 | 5688 | 58.7 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | " | 3603 | 447 | 831 | 1278 | 35.4 |
| 11 | ኦሮሚያ | " | 1373 | 568 | 670 | 1238 | 90.2 |
| | ድምር | | 45300 | | | 26314 | 58 |

**በ2000 በጀት ዓመት በክልሉ ሴክሬታሪያት በጀት የተመደበላቸው ማህበራት ብዛትና የገንዘብ መጠን**

| ተቁ | ዞን | የማህበራት ብዛት | የአባላት ብዛት | | | የተመደ በጀት መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | ባ/ዳር | 5 | 580 | 825 | 1405 | 496 275 |
| 2 | ደ/ጐንደር | 12 | 560 | 929 | 1489 | 1120040 |
| 3 | ሰ/ጐንደር | 16 | 795 | 1208 | 2003 | 1623480 |
| 4 | ሰ/ወሎ | 11 | 948 | 1329 | 2277 | 1844347.4 |
| 5 | ዋግኸምራ | 4 | 51 | 142 | 193 | 344675 |
| 6 | ደ/ወሎ | 21 | 40 | 900 | 961 | 1794000 |
| 7 | ኦሮሚያ | 4 | 340 | 270 | 614 | 482355 |
| 8 | ሰ/ሸዋ | 15 | 349 | 695 | 1059 | 1694193 |
| 9 | ምስ/ጐጃም | 17 | 1686 | 1040 | 2726 | 1619340 |
| 10 | ምዕ/ጐጃም | 14 | 320 | 902 | 1422 | 1505936 |
| 11 | አዊ | 8 | 170 | 383 | 553 | 735270 |
| 12 | በክልል ደረጃ | 3 | | | | 1090286 |
| | ድምር | 130 | 5839 | 8623 | 14462 | 13,853,922.4 |

## *2.2.2. የአለም ምግብ ኘሮግራም*

የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ ከመሄዱ ጋር በተለይ በከተሞች አካባቢ የምግብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል ። ይሄን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ታመው አልጋ ላይ የዋሉ ሰዎችና የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ በመሆን በአጭር ጊዜ ጤንነታቸው በመመለሱና ምርታማ ዜጐች እንዲሆኑ የዓለም ምግብ ኘሮግራም የአልሚ ምግብ በ4 የዞን ከተሞች እያቀረበ ይገኛል።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ኘሮግራሙ በሚካሄድባቸው አራት ከተሞች 2451 ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው የኤድስ ህሙማንና 6970 ወላጆቻቸዉን ያጡ ህጻናት በድምሩ 9421 ሰዎች የአልሚ ምግብ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በዚህ ኘሮግራም ተጠቃሚ የሆኑት ህመም የፀናባቸው ለመስራት አቅማቸው የደከመ የኤድስ ታማሚዎች ሲሆኑ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት መውሰዳቸውን በመቀጠል ከህመማቸው አገግመው ስራ እንዲጀምሩ ከተረጂነት መንፈስም እንዲላቀቁ በማህበራት በኩል በሚካሄደው የገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሳተፉ ጥረት እየተደረገ ነው። በተደረገው ድጋፍም የህሙማን

ሞት መቀነስ፣ የቤት ለቤት ክብካቤ መሻሻል እንዲሁም ህሙማን የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ እገዛ አድርጓል፡፡

**በ2000 የበጀት ዓመት በአለም የምግብ ኘሮግራም በባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴና ደ/ብርሃን የድጋፍና ክብካቤ ተጠቃሚች**

| ቁቁ | የተጠቃሚች አይነት | የተጠቃሚች ብዛት | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ባ/ዳር | | | ጎንደር | | | ደሴ | | | ደ/ብርሃን | | | ጠ/ድምር |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| 1 | ቫይረሱ በደማቸው ያለና የኤድስ ህሙማን | 256 | 625 | 881 | 166 | 534 | 701 | 206 | 410 | 657 | 42 | 170 | 212 | 2451 |
| 2 | ወላጆቻቸዉን ያጡ ህጻናትና ልጆች | 1081 | 1197 | 2278 | 1092 | 1048 | 2140 | 897 | 959 | 1856 | 295 | 401 | 696 | 6970 |
| 3 | የቤት ለቤት እንክብካቤ ሰጪች | 86 | 60 | 146 | 23 | 94 | 113 | 19 | 86 | 106 | 7 | 19 | 26 | 291 |
| 4 | ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል | | 50 | 50 | | 48 | 48 | | 50 | 50 | | 15 | 15 | 163 |
| ድምር | | 1454 | 1901 | 3267 | 1299 | 1691 | 2987 | 1122 | 1505 | 2669 | 344 | 605 | 949 | 9772 |

## *2.2.3. የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አገልግሎት*

ክልላችን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በሚያስፈልጋቸው ሰዎች ብዛት ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ በመሆኑ አገልግሎቱን በስፋት ማዳረስ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይሄን አገልግሎት ለማዳረስ የጣቢያዎችን ቁጥር መጨመር፣ የሰው ኃይል ማሰልጠንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ማከናወን ከዚህም ጋር የመድሃኒቱ ተጠቃሚዎች ያለማቋረጥ እንዲጠቀሙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡

በ2000 ዓ.ም በ3ኛው ምዕራፍ የተካሄደው የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻ የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከልና የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አገልግሎቶችን በመጠቀም ረገድ ከፍተኛ ውጤቶችን አስገኝተዋል፡፡ ባለፉት አመታት ለክልሉ ህብረተሰብ የተካሄዱት የግንዛቤ ማስጨበጫና የማህበረሰብ ውይይት ያስገኙት ለውጥ ትርጉም የሚሰጠው የነበር ቢሆንም በዚህ የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻ የተካሄደው የህዝብ ንቅናቄ ተግባራት ህብረተሰቡን የአገልግሎቶች ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

በዚህ በጀት ዓመት አገልግሎቱ በ17 ሆስፒታሎችና በ60 ጤና ጣቢያዎች በድምሩ 77 የጤና ተቋማት የተሰጠ ሲሆን 23,000 ያህል ሰዎችን አዲስ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ

ለማድረግ ታቅዶ 24,110 ያህል ሰዎች ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን ከታቀደው 105 % ተፈፃሚ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ 1215 ያህሉ ዕድሚያቸዉ ከ15 ዓመት በታች ናቸዉ።

እየተካሄደ ባለው የ3ኛው ምዕራፍ የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻን በመጠቀመ ለቅድመ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት እንዲሁም ለፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚነት አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸውን ሰዎች ሁሉ ለማዳረስ ታቅዶ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡

በዚህም መሠረት የፀረ-ኤች አይ ቪ መድኃኒት ህክምና ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ 48,986 ሰዎች የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆናቸው ልጆችና ህፃናት ቁጥር 5000 እንደሚደርስ ቢገመትም የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት የህፃናትና ልጆች ህክምና አገልግሎት በሆስፒታል ብቻ ተወስኖ በመቆየቱና ህብረተሰቡ ህፃናትና ልጆችን የማስመርመርና ፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ግንዛቤው የሚፈልገውን ያህል ባለመሆኑ ችግሩ እየጎላ መጥቷል። እስከ አሁን ድረስ በክልሉ 1965 ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆናቸው ልጆችና ህፃናት የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ ሆነዋል ።

## በ2000 በጀት አመት ፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አጠቃቀም በዞን ደረጃ

| ዞን | መለኪያ | ዕቅድ | የ2000 በጀት አመት | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክንዉን | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | በ2000 አዲስ የአገልግሎት ተጠቃሚች | | | TB/OIs/STIs የታከሙ | | | ART ጀምረው ያቋረጡ | | | ART መጠቀም ጀምረው የሞቱ | | | ከ15 ዓመት በታች ART የጀመሩ | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ባ/ዳር | በቁጥር | ***3298*** | **3843** | **3767** | **7610** | **336** | **278** | **614** | 152 | 152 | 304 | 73 | 86 | 159 | | | |
| ምዕ/ጉጃም | " | **1633** | **376** | **590** | **966** | 2 | 1 | 3 | - | - | - | - | - | - | | | |
| አዊ | " | ***730*** | **149** | **243** | **392** | 477 | 748 | 1222 | 1 | 3 | 4 | 4 | 6 | 10 | | | |
| ምስ/ጉጃም | " | **3773** | **638** | **873** | **1511** | - | - | - | 75 | 50 | 125 | - | - | | | | |
| ሰ/ሸዋ | " | **4966** | **881** | **1336** | **2217** | 414 | 477 | 891 | 33 | 46 | 79 | 23 | 47 | 70 | | | |
| ኦሮሚያ | " | **412** | **298** | **369** | **667** | 135 | 240 | 375 | 25 | 31 | 56 | 35 | 39 | 74 | | | |
| ደ/ወሎ | " | **2061** | **1469** | **2022** | **3491** | - | - | - | - | - | - | - | | | | | |
| ሰ/ወሎ | " | **1812** | **723** | **1021** | **1744** | 314 | 367 | 681 | 20 | 10 | 30 | 21 | 20 | 41 | | | |
| ዋግኽምራ | " | **855** | **114** | **145** | **259** | 75 | 69 | 144 | - | - | 107 | 0 | 3 | 3 | | | |
| ደ/ጎንደር | " | **4044** | **860** | **1170** | **2030** | - | - | - | 17 | 21 | 38 | 10 | 16 | 26 | | | |
| ሰ/ጎንደር | " | **5000** | **1429** | **1794** | **3223** | - | - | - | - | - | - | - | | | | | |
| ድምር | " | **23000** | **10780** | **13330** | **24110** | **1753** | **2180** | **3930** | **323** | **313** | **743** | **166** | **214** | **380** | | | **1215** |

**ማሳሰቢያ፤** አጠቃላይ የፀረ ኤች አይ ቪ መድኃኒት በክልሉ የጀመሩ ሰዎች 48986 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 1965 ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ናቸው፡፡

## 2.2.4. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የሚደረግ ድጋፍ

በክልሉ ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ/ኤድስና በሌሎች ምክንያቶች የሚያጡ ተጋላጭ ልጆች ቁጥር ከሚደረገው የድጋፍና ክብካቤ ምላሽ በላይ በመሆኑ በርካታ ህፃናት ለጎዳና ህይወትና ሌሎች ችግሮች እየተጋለጡ ይገኛሉ:: የነዚህ ልጆች ችግሮች ዘላቂታዊ መፍትሄ የሚሹ ቢሆኑም በክልላችን የሚገኙ አጋር ድርጅቶችና ፈፃሚ አካላት ከተለያዩ ምንጮች በሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ ለጥቂቶቹ የመሠረታዊ ፍላጐትና የትምህርት ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ::

በበጀት ዓመቱ በድምሩ 67,700 ያህል ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች የመሠረታዊና የትምህርት ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም የተወሰኑትን በገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲደገፉ ታቅዶ በበጀት አመቱ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተደርጓል::
የመሠረታዊና የትምህርት ድጋፎች አንዲሁም የገቢ ማስገኛ ተግባራት ወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ ልጆች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉና ጤናማ ዜጐች እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል::

በዚህም መሠረት በዚህ የበጀት ዓመት 107,803(159.2%) ያህል ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የመሠረታዊና የትምህርት ድጋፍ የተደረገ ሲሆን 4004 ያህሉ በገቢ ማስገኛና ጥቃቅን ንግድ ስልጠና አግኝተው በጥቅሉ 15,426 ያህል ልጆች በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ተሰማርተዋል:: ተግባራት ማስፈጸሚያ ከክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ብር 23,621,562.00 በመመደብ ለየዞኖች ተልኳል::

በተለያዩ ረጂ ድርጅቶችና ፈፃሚዎች ከሚከናወነው የድጋፍና ክብካቤ ጎን ለጎንም ህብረተሰቡ ለችግሩ ምላሽ በባለቤትነት በመውሰድና አቅሙን በማጎልበት በድጋፍና እንክብካቤው ተግባራት ተሳታፊነቱን እያጎላ ይገኛል::ለምሳሌ:
በክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት እና ለዉጥ በህብረት በሚባል አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ትብብር በክልል ደረጃ 19 ቢሮዎች 78 ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ሠራተኛዉ በባለቤትነት እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ትምህርታቸውን አስከሚጨርሱ በባለቤትነት ለማሳደግ የተረከቡ ሲሆን በ2001 በጀት አመት ሌሎች ቢሮዎችና መ/ቤቶች ተመሳሳይ ድጋፍ እንዲሰጡ ታቅዷል :: ይህ ተግባር በዓርዓያነቱ ወደ ወረዳና ዞንም መስፋፋትና መተግበር ያለበት ጥሩ ጅምር ነዉ::

## በ2000 በጀት ዓመት ወላጆቻቸውን ላጡና ለኤች.አይ.ቪ ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት የተደረገ ድጋፍ በዞን ደረጃ

| ተ.ቁ | ዞን | ዓመታዊ ዕቅድ | ዓመታዊ አፈፃፀም | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መሠረዊና የትምህርት ድጋፍ ያገኙ | | | በገቢ ማስገኛና ጥቃቅን ንግድ የሰለጠኑ | | | በገቢ ማስገኛ የተሰማሩ | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ባ/ዳር | **18348** | 11739 | 10638 | 22377 | 84 | 78 | 162 | 1472 | 1486 | 2958 |
| 2 | ምዕ/ጐጃም | **3439** | 2007 | 1337 | 3344 | 300 | 447 | 747 | 502 | 460 | 962 |
| 3 | አዊ | **3582** | 975 | 779 | 1754 | 217 | 186 | 403 | 219 | 189 | 408 |
| 4 | ምስ/ጐጃም | **5396** | 3032 | 2553 | 5585 | 872 | 853 | 1715 | 875 | 856 | 1721 |
| 5 | ሰ/ሸዋ | **7488** | 4463 | 4289 | 8752 | 73 | 79 | 152 | 714 | 568 | 1282 |
| 6 | ኦሮሚያ | **1909** | 1091 | 954 | 2045 | 209 | 189 | 389 | 551 | 428 | 985 |
| 7 | ደ/ወሎ | **12113** | 25795 | 26940 | 52735 | 0 | 0 | 0 | 1455 | 2035 | 3718 |
| 8 | ሰ/ወሎ | **3069** | 779 | 608 | 1387 | 120 | 96 | 216 | 354 | 292 | 646 |
| 9 | ዋግኽምራ | **963** | 423 | 590 | 1013 | 96 | 124 | 220 | 120 | 139 | 284 |
| 10 | ደ/ጎንደር | **5539** | 1876 | 1659 | 3535 | 0 | 0 | 0 | 620 | 592 | 1212 |
| 11 | ሰ/ጎንደር | **5854** | 2540 | 2736 | 5276 | 0 | 0 | 0 | 610 | 640 | 1250 |
| 12 | ድምር | **67700** | **54720** | **53083** | **107803** | **1971** | **2052** | **4004** | **7492** | **7685** | **15426** |

## 2.3. የአቅም ግንባታ ተግባራት

በክልሉ የሚካሄዱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት በታቀደው መልኩ እንዲፈፀሙ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ተግባራትን በየደረጃው ማካሄድ አስፈላጊ ተግባር በመሆኑ ባሳለፍነው ዓመት በርካታ የአቅም ግንባታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. የጤና ተቋማት ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና መቆጣጠር አቅማቸውን ማጎልበት ትኩረት የተሰጠው ተግባር በመሆኑ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት በበጀት ዓመቱ ተከናውነዋል፡፡
   - የሦስት አዳዲስ የኤች አይ ቪ ምርምራ ማዕከላት ግንባታ፣
   - ለኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ ማዕከላት ቁሳቁስ ማሟላት፣
   - ለ26 የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና በሚሰጥባቸው ተቋማት የእድሳትና ቁሳቁስ ማሟላት፣
   - የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና አገልግሎት በሚሰጥባቸው የጤና ተቋማት ዳታ ክለርክ ቅጥር ማካሄድ፣
   - ለክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ የኮምፒዮተር ስፔሻሊስት መቅጠር የሚሉት ናቸው

2000 በጀት አመት በት/ቤቶችና ከት/ቤቶች ውጪ የመረጃ ማዕከላት፣ ሚኒ ሚዲያዎችና ፀረ ኤድስ ክበባት መመስረትና ማጠናከር በዞን ደረጃ

| | | በት/ቤት የመረጃ መዕከላትና ሚኒሜዲየዎችን ማቋቋምና መጠነከር | | | ከት/ቤት ወጪ የመረጃ መዕከላትና ሚኒሜዲየዎችን ማቋቋምና መጠነከር | | | በት/ቤት የፀረ ኤድስ ክበባተን መመስረትና ማጠናከር | | | ከት/ቤት ዉጪ የፀረ ኤድስ ክበባተን መመስረትና ማጠናከር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ዞን | ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር % | ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር % | ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር % | ዕቅድ | ክንውን | ንፅፅር % |
| 1 | ባህርዳር | 5 | 5 | 100 | 3 | 2 | 66.67 | 26 | 26 | 100 | 22 | 22 | 100 |
| 2 | ምዕ/ጎጃም | 87 | 75 | 86.2 | 0 | 0 | 0 | 329 | 252 | 76.60 | 65 | 47 | 72.31 |
| 3 | የአዊ | 64 | 67 | 104.7 | 5 | 11 | 220 | 300 | 252 | 84 | 122 | 85 | 69.67 |
| 4 | ምስ/ጎጃም | 20 | 20 | 100 | 17 | 17 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ሰ/ሸዋ | 148 | 47 | 31.76 | 50 | 45 | 90 | 148 | 225 | 152.03 | 50 | 40 | 80 |
| 6 | ኦሮሚያ | 18 | 9 | 50 | 10 | 5 | 50 | 142 | 29 | 20.42 | 16 | 9 | 56.25 |
| 7 | ደ/ወሎ | 11 | 13 | 118.18 | 12 | 6 | 50 | 242 | 149 | 61.57 | 154 | 158 | 102.60 |
| 8 | ሰ/ወሎ | 29 | 4 | | 30 | 3 | 10 | 201 | 129 | 64.18 | 106 | 106 | 100 |
| 9 | የዋግ ብ/ሰብ | 46 | 48 | 104 | 22 | 21 | 95.45 | 134 | 155 | 115.67 | 30 | 45 | 150 |
| 10 | ደ/ጎንደር | 0 | 0 | | 22 | 9 | 40.91 | 40 | 40 | 100 | 0 | 0 | 0 |
| 11 | ሰ/ጎንደር | 12 | 24 | 200 | 19 | 18 | 94.74 | 222 | 158 | 71.17 | 15 | 7 | 46.67 |
| | ድምር | 440 | 312 | 0 | 190 | 137 | 72.1 | 1784 | 1415 | 79,32 | 580 | 519 | 89.48 |

2. የማህበረሰብ አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ አማካሪዎችን አሰልጥኖ ማሰማራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘ ቱ 146 ኮሚኒቲ ካውንስለሮች ሰልጥነው እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡
3. የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ተግባራትን የማጠናከር ተግባር ተከናውኗል፡፡
4. የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መረጃ ማዕከልን አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስ ግዢ ተደርጓል፡፡
5. በክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ሥር የሚገኙ ለ11 የዞንና ለ150 የወረዳ መስተባበሪያ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ለክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት በድምሩ 166 ዴስክቶፕ ኮምፒዊተሮች ፣177 ፕሪንተር ፣ 9 ፎቶ ኮፒ ማሽን ፣ 12 ኦልሲዲ ፕሮጀክተር ፣ 13 ላፕቶፕ ኮምፒዉተሮች፣ 9 ቴሌቪዥን ፣ 14 ዲቪዲ ፣ 10 ዲሽ ለማህበራትና ክበባት ተሰጥቷል ፡፡ 4200 ሬዲዮንችን ለአርሶ አደሩ ለማሰረጨት ግዝ ሂደቱ በመጠናከቅቅ ላይ ነዉ ፡፡
6. ክልሉን የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆጣጠር ተግባራት በየደረጃው ለማጠናከር የሚያግዙ አምስት የአፈፃፀም መመሪያዎች በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው በክልልና በየዞኖቹ ለሚመለከታቸው አካላት ትውውቅ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጁትም የኘሮጀክት አስተዳደር፣ የፋይናንስ፣ የግዢ፣ የክትትልና ግምገማ እንዲሁም የኘሮጀክት አስተዳደር መመሪያዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የማህበረሰብ ንቅናቄ ኘሮግራሞች አፈፃፀምና መመሪያ በድምሩ 3,258 ኮፒዎች ስልጠና ለተካፈሉና ለሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶች ተከፋፍሏል፡፡
7. በጎንደርና ደሴ በብሄራዊ ኤች አይ ቪ/ኤድሰ መከ/መቆ/ጽ/ቤት በብሔራዊ ኤድስ መረጃ ማዕከልና በሲዲሲ ኢትዮጵያ ድጋፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መረጃ ማዕከላት የኔት ወርክ ተከላና አስፈላጊዉ ቁሳቁስ ተሟልቶላቸዉ በበጀት አመቱ መጨረሻ ወር ላይ ተመርቀዉ የተከፈቱ ሲሆን በአሁን ወቅት መረጃ ማዕከላቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸዉ፡፡
8. የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱንና የአጋር ድርጅቶችን አቅም ለማጎልበትና የተሻሉ የአሠራር ተሞክሮዎችን ለማየት ከወረዳ፣ ከዞን፣ ከክልል የኤች አይ ቪ /ኤድስ ሴ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የሴክተር መ/ቤቶችና የዞን አስተዳደር አመራሮችን በድምሩ 37 አባላት በሶስት ዙር የዩጋንዳ ጉብኝት አድርገዋል፡፡
9. የ2001 የበጀት ዓመት አሳታፊ የጋራ ዕቅድ ዝግጅት በክልል ደረጃ በርካታ አጋር ድርጅቶችና ሴክተር መ/ቤቶች በሚገኙበት ተካሂዷል፡፡ ይሄው አሳታፊ የጋራ ዕቅድ ዝግጅት በዞኖችና ወረዳዎች እስከ ቀበሌ ድረስ በተመሳሳይ መልኩ ተካሂዷል፡፡
10. የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አወሳሰድን ከማህበረሰብ ንቅናቄ በተለይም ከማህበረሰቡ ውይይት ጋር አቀናጅቶ መስራት ስለሚቻልበት ሁኔታ ከአሜሪካን ሚቺጋን ስቴት የመጡ ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡ የሚቺጋን ስቴት በሰጠዉ የጉብኝት እድል ከክልሉ

ሴክሬታሪያት ጽ/ቤትና ከክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት 3 ሰዎች በአሜሪካ ሚቺጋን ስቴት የልምድ ልዉዉጥ አድረገዉና በክልሉና በሚችጋን ስቴት የትስስር መድረክ ተካሂዷል፡፡

11. እየተካሄዱ ያሉትን የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን የሚያግዙ በርካታ ስልጠናዎች በተለያዩ አካላት ይሰጣሉ፡፡ በ2000 በጀት አመት በክልሉ ሁሉም ዞኖች የተሰጡት ዋና ዋና ስልጠናዎች ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

## በ2000 የበጀት ዓመት በዞኖች የተከናወኑ ስልጠናዎች

| ተቁ | የስልጠናው አይነት | መለኪያ | 2000 በጀት አመት ክንውን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | የቤት ለቤት እንክብካቤ | ቁጥር | 595 | 646 | 1241 |
| 2 | አቻ ለአቻ | " | 1347 | 784 | 2131 |
| 3 | የገቢ ማስገኛ | " | 1049 | 2152 | 3201 |
| 4 | የሕይወት ክህሎት | " | 8177 | 6001 | 14178 |
| 5 | የክበብ አመራር | " | 691 | 513 | 1204 |
| 6 | ሜይንስትሪሚንግ | " | 800 | 457 | 1257 |
| 7 | አመራር | " | 1540 | 268 | 1808 |
| 8 | የማህበረሰብ ውይይት አመቻቾች | " | 924 | 2296 | 3220 |
| 9 | የማህበረሰብ ውይይት ተሣድሶ | " | 468 | 1432 | 1900 |
| 10 | የባህሪ ለውጥ ስርፀት | " | 4020 | 2434 | 6454 |
| 11 | የኘሮጀክት ዝግጅና አስተዳደር | " | 403 | 374 | 777 |
| 12 | ጉጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና ኤች አይ ቪ/ኤድስ | " | 4696 | 4600 | 9296 |
| 13 | ኮሚኒቲ ካውንስሊግ | | 113 | 149 | 262 |
| 14 | ስነ ተዋልዶ ጤና፣ ስነ ፆታና ኤች አይ ቪ/ኤድስ | " | 470 | 622 | 1092 |
| 15 | ኤች አይ ቪ/ኤድስና ሰብዓዊ መብት | " | 233 | 129 | 362 |
| 16 | የህጻናት መብት | " | 270 | 297 | 567 |
| 17 | የማህበረሰብ አቀፍ ኘሮግራሞች | " | 995 | 1712 | 2707 |
| 18 | የወጣቶች ውይይት | " | 91 | 84 | 175 |
| 19 | ፖዘቲቭ አኗኗር | " | 448 | 268 | 716 |
| | ድምር | | 27,330 | 25,218 | 52,548 |

<u>ሌሎች ዓወደ ጥናቶችና ሴሚናሮች</u>

⇒ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የ2000ዓ.ም ከ1000 በላይ ተመራቂ ተማሪዎች

⇒ ለመምህራን ማህበር በዓመታዊ ጉባኤ ለተገኙ ከ200 በላይ ለሚሆኑ

⇒ የትምህርት ቢሮው ያዘጋጀው የሚሊኔም ፌስቲቫል ላይ ለተገኙ ከ1200 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች

⇒ የሐይማኖት አባቶች በተለይም የኦርቶዶክስ ተዋህዶና የእስልምና እምነት ተከታዮች 70 ለሚሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለ3 ቀን ከሲቪኤም ጋር በመተባበር ተሰጧል፡፡

⇒ ለ25 የምዕራብ ዕዝ ጤና ባለሙያዎች በኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ለ21 ቀን የካውንስሊንግ ስልጠና ተስጧል፡፡

⇒ ከ200 በላይ ለሚሆኑ ጤና ባለሙያዎች በኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት በአዲሱ አልጎሪዝም ስልጠና ተሰጧል፡፡

**በ2000 የበጀት ዓመት በክልል ደረጃ በተለያዩ አጋር ድርጅቶች የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችና አውደ ጥናቶች**

| ተቁ | የተከናወኑ የስልጠና/አውደ ጥናት አይነቶች | የተሳታፊ ብዛት | የሥልጠናው/ አውደ ጥናት ቀን ብዛት | የተሳታፊው ክፍል/ድርጅት | ድጋፍ ያደረገው ድርጅት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የEMSAP-II ማስተዋወቂያ ወርክሾኘ ላይ መሣተፍ | 2 | 3 | ክልል ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት | ፌዴራል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት |
| 2 | የህዝብ ንቅናቄ ስትራቴጂ የአሰልጣኞች ስልጠና | 5 | 8 | ከክልልና ዞን ሴክ/ ጽ/ቤቶች፣ ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ | ፌዴራል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት |
| 3 | የEMSAP-II ማስተዋወቂያ ወርክሾኘ | 60 | 3 | የዞን ማስ/ጽ/ቤቶች፣ የዞን ጤና መምሪያዎች የክልል ሴክተር መ/ቤቶች መያድ | ክልል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክ/ጽ/ቤት |
| 4 | መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ስልጠና | 155 | 6 | የማህበራት አመራር አባላት | ክልል ጥምረት |
| 5 | የሴክተር መ/ቤቶች የ2000 የበጀት ዓመት ዕቅድ አውደ ጥናት | 32 | 2 | የሴክተር መ/ቤቶች | ክልል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክ/ጽ/ቤት |
| 6 | የህይወት ክህሎት የአሰልጣኞች ስልጠና | 280 | 7 | መምህራን | ክልል ኤች አይ ቪ/ኤድስ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መከ/መቆ/ሴክ/ጽ/ቤት |
| 7 | የማህበረሰብ ውይይት የአሰልጣኞች ስልጠተና ተሃድሶ | 160 | 3 | ከየዞኑ የተውጣጡ አመቻቾች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤት/UNFPA |
| 8 | ስትራቴጂክ ሊደርሺኘና ኮሚኒኬሽን | 1 | 12 | ከክልል ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት | ፌዴራል ሴክሬታሪያትና ጆንሆኘኪንስ ዩኒቨርስቲ |
| 9 | Standards based managment recognition | 275 | 7(2 ዙር) | የጤና ባለሙያዎች የስራ ላይ ስልጠና | JHPIEGO እናጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 10 | በሶሻል ሞቢላይዜሽን (ሜይንስትሪሚንግ፣ የበጎ ፈቅድ አገልግሎት፣ ክትትልና ግምገማ) ክልላዊ የአሰልጣኞች ስልጠና | 66 | 5 | ከዞን ሴክተር መ/ቤቶችና ማስ/ጽ/ቤቶች | የክልለ ሴክ/ጽ/ቤት |
| 11 | ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ሴቶች የአመራር ስልጠና | 110 | 5 | ከዞኖች የተውጣጡ የማህበር አመራሮች/አባላት | UNFPA/ ክልል ሴክ/ጽ/ቤት |
| 12 | የቤት ለቤት ክብካቤ ተሃድሶ | 345 | 5 | ከዞኖች የተውጣጡ የቤት ለቤት ክብካቤ ሰጪዎች | WFP/ ክልል ሴክ/ጽ/ቤት |
| 13 | የኤች/አይቪየደም ምርመራናየምክር አገልግሎት | 268 | 7 | ከጤና ጣቢያ የተመለመሉ ባለሞያዎች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 14 | አዲሱን የኤች አይቪ የደም ምርመራ ዘዴ | 305 | 7 | ከጤና ጣቢያ የተመለመሉ ባለሞያዎች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 15 | የፀረ ኤች ኣይቪ መዳህኒት አገልግሎት አሰጣት | 198 | | ከጤና ጣቢያ የተመለመሉ ባለሞያዎች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 16 | ሁሉን አቀፍ ህክምናና እንክብካቤ | 133 | | ከጤና ጣቢያ የተመለመሉ ባለሞያዎች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 17 | በህክምና ላይ የኤች አይቪ የደም ምርመራ | 111 | | ከጤና ጣቢያ የተመለመሉ ባለሞያዎች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 18 | የአባለዘር በሺታዎች ህክምና አሰጣጥ | 41 | | ከጤና ጣቢያ የተመለመሉ ባለሞያዎች | ክልል ሴክ/ጽ/ቤትና ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 19 | የበጎ ፍቃደኞች ፀረ ኤች አይቪ ኤድስ መልክተኞች የአሰልጣኞች ሥልጠና | 82 | | ከ ሴክተሮች የተዉጣጡ ባለሞያወች | ክልል ሴ/ጽ/ቤት |
| 20 | ቀበሌ ተኮር የኤች አይቪ ኤድስ አግልገሎት ሰጭዎች | 280 | | ከማህበረሰቡ የተዉጣጡ ወጣቶች | ጤና ጥበቃ ቢሮ |
| 21 | ወላጆቻቸዉን ላጡ ህጻናት የምክር አገልገሎት አሰጣት | 100 | | ከማህበረሰቡ የተዉጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎች | ክልል ሴ/ጽ/ቤት |
| | ድምር | 3009 | | | |

## በጠበልና የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሐኒት አጠቃቀምና ችግሮች ዙሪያ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት አባቶችና የምእነቱ ተከታዮች ጋር የተደረገ ዓውደ ጥናት

የክልሉ ኘሬዚዳንት የክልሉ አበው ሊ.ቃነ ጳጳሳትና የሥራ ኃላፊዎች፣ የየሃገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆችና የስብከተ ወንጌል ሃላፊዎች፣ የየሃገረ ስብከቱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቅርንጫፍ አስተባባሪዎች፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተወካዬች፣ የልማት ኮሚሽን ኮሚሽነርና ሠራተኞች እንዲሁም አጥማቂዎች 80 ተሳታፊዎች በተገኙበት በጠበልና የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሐኒት አጠቃቀምና ችግሮቹ ዙሪያ ለአንድ ቀን ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡በዚህም መሠረት አቋም አስቀምጠዋል፡፡ይኸውም

ከሃያ ሦስት ዓመታት በፊት በዓለማችን የተከሰተው ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሃይማኖትንና ፖለቲካን ሳይለይ፣ የፆታ የዘርና የቀለም ልዩነት የዕድሜም ገደብ ሳያደርግ፣ የሃገርም ድንበር ሳይወስነው የሰው ዘር ሁሉ ደምሳሽ ጠላት መሆኑን ቤተ ክርስቲያን በመገንዘብ የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት ለመከላከል ከተሰለፉት መንግሥታዊያንና መንግሥታውያን ካልሆኑ በጎ አድራጊዎች ድርጅቶች አንድዋ ቅድስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጆችን ቅስም ሰባሪና ሕይወት አጥፊ የሆነውን ኤድስን ለመዋጋት በአላት ኃይል ሁሉ በመንቀሳቀስ ላይ ስትሆን ልጆችዋ ሁሉ ከዚህ በሽታ እንዲጠበቁ በየጊዜውም ያለ ጊዜውም ትመክራለች፣ ታስተምራለች፣ ታስጠነቅቃለች፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ብቻ ሳይሆን ከሞት በፊት በዚህ ዓለም ስላለው ሕይወትም ስለምታስጠነቅቅ ልጆችዋ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም መልካም ሕይወት እንዲኖራቸው ነገረ ሕይወትን ከማስተማር የተቆጠበችበት ጊዜ የለም አይኖርምም፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ መንስዔና መስፋፊያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጤና ባለሙያዎች የሰጧቸውን ምክንያቶች ከመቀበል በቀር ሌላ ምክንያት የላትም፡፡ ይኸውም ሕገ እግዚአብሔርን ካለመጠበቅና ከአንደንድ ጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ በሽታው የሚተላለፍ መሆኑ ነው፡፡

በሽታውን ስለመከላከልም ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ ቅድመ ጋብቻ በንጽሕና መኖርና መወሰንን ታስተምራለች፡፡

ኤች አይ ቪ ኤድስም ሆነ ሌላው በሽታ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣና መቅሰፍት መርገምና ቅጣት እንዲሁም የኃጢአት ዋጋ እንደሆነ አድርጋ አታስተምርም፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ «የእግዚአብሔር» ሥራ እንዲገለጥበት እንጂ ራሱ በሽተኛው አልበደለም፡፡ ወላጆችም አልበደሉም በማለት በሽታ እንደቅጣት ፍርድ ነው ብለው ይገምቱ የነበሩ የተናገረው ቃል

ሕሙማን ሁሉ ኃጢአተኞች አለመሆናቸውን፣ በሽታውም የኃጢአት የቅጣት ፍርድ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በሽታ በኃጢአት ጤናም በደግነት ቢሆን ኖሮ ዓለም በሙሉ በበሽታ ባለቀ ነበር፡፡ አንድም ከኃጢአት የራቀ ጻድቅ የለምና፡፡
በሽታ ኃጢአት ነው፣ በሽተኞችም ኃጢአተኞች ናቸው የሚለው አስተሳሰብ የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ይቃወማል፡፡ ምክንያቱም ኃጢአትን የሚያስተሰርይ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ቫይረሱ የሌለበትና የኤድስ ሕሙም ያልሆነም በዚህ ብቻ ከኃጢአት ንጽሑ ነው የሚል ትምህርትና እምነት በቤተ ክርስቲያኒቱ የለም፡፡

በአሁኑ ጊዜ የፀረ ኤች አይ ቪ መድኃኒት እየተሰጠ መሆኑ የታወቀ ነው መድኃኒቱ የሕይወት መጠበቂያና መደገፊያ እስከ ሆነ ድረስ እንደ ምግብ ሊቆጠር ይችላል፡፡

ከበሽታቸው ለመዳን ፈልገው የሚመጡትን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ታስተናግዳቸዋለች ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ በባለ መድኃኒት ወይም በሐኪም ተፈቅዶና ታዝዞ በሚሰጠው መድኃኒት የእግዚአብሔር አዳኝ እጅ እንዳለ ታምናለች ቅዱስ የእግዚአብሔር የአዳኝነቱ ኃይል የሚገለጥበት መሆኑን አምና ታስተምራለች፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕሙማን እግዚአብሔር በሁሉም ማዳን እንደሚችል አምነው መድኃኒቱን እንዲወስዱ በጠበልም እንዲጠመቁ ቢፈልጉ አትከለክልም፡፡ በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን ምክንያት ስለሚሻ በጠበል፣ አጥማቂውና በባለ መድሃኒቱ ይጠቀማል ሐኪሙም የእርሱ የማዳን ምክንያቶች ናቸውና የሥርዓቱን ቅደም ተከተል በመጠበቅ በሁሉም መጠቀም እንደሚቻል ትመክራለች፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከሉና በመቆጣጠሩ እንቅስቃሴ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ መገኘቷ የሚታወቅ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ትውልድ እንዳያልቅ፣ አድሎና መገለል እንዳይኖር፣ በመታቀብና በመታመን እንዲኖር እንዲሁም እራሱን ከኤች አይ ቪ/ኤድስና ከመሳሰሉት በሽታዎች እንዲጠብቅ በማስተማር ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህም መሠረት በአውደ ጥናቱ ማጠቃለያ ላይ ያቋም መግለጫ አውጥተዋል፡፡

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት “በፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒቶች አሰጣጥና አጠቃቀም ሂደት የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮች ሲምፖዚየም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት፣ ከጤና ጥበቃ ቢሮ የአይቴክ ኢትዮጵያና የዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል በጋራ በመሆን በፀረ-ኤች አይ ቪ ሕክምና አሰጣጥና አጠቃቀም ሂደት የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮችን በመገምገም የወደፊት አቅጣጫ ለማመላከት ከመስከረም 27 -28/2000 የፀረ ኤች አይ ቪ መድሐኒት የሚሰጡ 41 የጤና ጣቢያ ኃላፊዎች፣ 17 ሆስፒታሎችና በዚሁ ጉዳይ የሚመለከታዉ ሌሎች የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የቢሮ ኃላዎች በተገኙበት ለሁለት ቀናት  የቆየ ሲፖዚየም ተካሂዷል፡፡

ከዚህም ባሻገር ባለፈው ዓመት የተጀመረው የሚሌኒየም የፀረ-ኤድስ ዘመቻ 3ኛ ምዕራፍ በይፋ የተጀመረበት ወቅት በመሆኑም ካለፉት ሁለት የዘመቻ ምዕራፎች ባካበትነው ልምድ በመነሣት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የዚህ ሲምፖዚየም ውጤት የጎላ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡

የኤች አይ ቪ ስርጭትና እያደረሰ ያለው ጉዳት ስፋትና ጥልቀት የሁሉንም የሐገሪቱ ክልሎች ያዳረሰ ቢሆንም የጉዳቱ መጠን በአንዳንድ ክልሎች ጎልቶ ይታያል፡፡ የአማራ ክልልም የኤች አይ ቪ ስርጭትና ጉዳት ጎልቶ ከሚታዩባቸው ክልሎች መካከል ይመደባል፡፡

ይህን ግዙፍ የኤች አይ ወረርሽኝ በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ የክልሉ መንግስት በተለይ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴ/ጽ/ቤት፣ ልዩ ልዩ ሴክተር ቢሮዎች፣ የሲቢክ ማህበራትና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች ማህበራት፣ ህብረተሰቡ፣ ለጋሾችና ተባባሪ ድርጅቶች ከፍተኛ ርብርቦሽ አድርገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ።

መልካም ውጤት ቢገኝም ችግሮችም ተስተውለዋል፡፡ ለምሳሌ የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና ሽፋን ለማስፋት እንቅስቃሴ በሚደረግበት ወቅት የጥራት ማነስ፣  የመድሃኒት፣ የላብራቶሪ ቴስት ኪቶችና ሪኤጀንቶች እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች አቅርቦት የተሟላ አለመሆኑ፣ በየደረጃው የአመራሩ የባለቤትነት ስሜት የሚፈለገውን ያህል አለመዳበሩ፣ የህብረተሰብ ተሣትፎ አለማደጉ፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የፀረ-ኤች አይ ቪ ሕክምና ተጠቃሚዎች

ሕክምናቸውን ማቋረጣቸው፣ የሠለጠነ የጤና ባለሙያዎች ከሥራ መልቀቅና እጥረት መፈጠሩ፣ በሥራ ጫና ምክንያት የባለሙያ የመሰላቸት (burn out) ሁኔታ መፈጠሩ እና ሌሎችም ተጠቅሰዋል፡፡ በመጨረሻም የአቋም መግለጫ በማውጣት ሲምፖዚየሙ ተጠናቋል፡፡ ከአማራ ክልል የፀረ-ኤድስ የሴቶች ጥምረት ከሴቶች ጉዳይ ቢሮ ከአማራ ሴቶች ማህበርና የሴ/ጽ/ቤት በጋራ የተካሄደው ጉባኤ ከ1200 በላይ ለሚሆኑ ህ/ተሰብ ከፍተኛ ንቅናቄ ተካሂዷል፡፡

## 2.4. ሜይንስትሪሚንግና ፓርትነርሽፕ

### *2.4.1. የመንግስት ሴክተሮች አፈፃፀም*

በየደረጃው ያለው የመንግስት ሴክተሮች ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከል በመቆጣጠር እንዲሁም በድጋፍና እንክብከቤ በመደበኛ ስራ አካቶ (ሜይንስትሪም አድርጎ) እንዲያከነውን ይጠበቃል፡፡ ከነዚህ ተግባራት ውስጥም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስራዎችን የሚያስተባብር ተጠሪ መመደብ በመ/ቤቱ በሁሉም የስራ ክፍሎች የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስራ እንዲታቀድና ተግባራዊ እንዲሆን ከመንግስት በጀት 2 በመቶ እንዲመደብ ሠራተኛው ለኤች አይ ቪ እንዳይጋለጥ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሰዎችና ለኤድስ ህሙማን እንዲሁም ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ድጋፍና እንክብከቤ ለማድረግ ኤድስ ፈንድ በማቋቋም እንደ መደበኛ ስራዎች በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ማድረግ እና የመሳሰሉትን ተግባራት ናቸው፡፡

በዚህ የበጀት ዓመት የሴክተሮች ዕቅድ አፈፃፀም ለመገምገማና የ2001 ዕቅድ ዝግጅት ለማካሄድ በክልል ደረጃ የሚገኙ ሴክተር መ/ቤተችን በመያዝ ውይይት ተደርጎአል፡፡ በዚህ ወርክሾፕ እንዲሳተፉ ከሚጠበቁት 43 ቢሮዎች 42 ቱ ተገኝተዋል፡፡ በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች ከወር ደመወዛቸዉ ከሚቆረጥ የተቋቋመው ኤድስ ፈንድ 90 ወላጅ ያጡ ሕጻናትና 12 ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ወገኖቻችንን ለእያንዳዳቸዉ በወር ከብር 150 —250 በመመደብ ህፃናትን አሳዳጊወችቻዉ እንደ ልጆቻቸዉ በመቁጠር እንዲከባከቧቸዉና እንዲያስተምሯቸዉ ርክክብ ተደርጓል ፡፡

በዞኖችና ወረዳዎች እየተከናወኑ የሚገኙ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ተግባራትን በሚመለከት 1319 በየደረጃው የሚገኙ የሴክተር መ/ቤቶችና 822 የገጠር ቀበሌዎች የኤድስ ፈንድ አቋቁመዋል፡፡ በተጨማሪም 1941 ሴክተር መ/ቤቶች ለኤች አይ

ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ወደ 2.9 ሚሊዮን የሚጠጋ ብር ከበጀታቸው 2% መድበዋል፡፡ የገጠሩ ህብረተሰብም እህል በማሰባሰብ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ የጎላ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡

## *2.4.2. ፓርትነርሽፕ (አጋርነት)*

1. ክልላዊ የፀረ-ኤች አይ ቪ/ኤድስ የአጋርነት መድረክ ጠቅላላ ጉባኤ ተካሂዷል፡፡ ጉባኤው ከዚህ በፊት ከተካሄደው ልዩ የሚያደርገው የእያንዳንዱ ፎረም ተወካዮች በየፎርማቸው ተወክለው የመጡበት፣ የዞኖች ጥምረትና ጅምያ ተወካዮች ከየዞን መጥተው የተገኙተና አስተሳሳሪ ኮሚቴዎች የተመረጡበት በመሆኑ ነው፡፡
2. ንዑሳን የትብብር ፎረሞችን በተመለከተ

**የመንግስታዊ ድርጅቶች የፀረ-ኤች አይ ቪ/ኤድስ መድረክ /ፎረም/**

- የፎረሙ የአስተባባሪ ኮሚቴዎች ስምንት መደበኛ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፡፡
- መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ተካሂዷል፡፡
- የ3 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቶአል በሁሉም አባል መ/ቤቶች ተልኮ ተሰጧል፡፡
- የፎረሙ ዓመታዊ የሥራ እቅድ ወጥቷል፡፡
- አዲስ የፎረም የአስተባባሪ ኮሚቴዎች ምርጫ ተካሂዷል፡፡
- ከክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት በተገኘ ድጋፍ 32 የመንግስት መ/ቤቶች ተወካዮች የኤች አይ ቪ ሜይንስትሪሚንግ ስልጠና አግኝተዋል፡፡
- በክልላዊው የትብብር መድረክ 5 ተወካዮች ተመርጠው ተሳትፈዋል፡፡

**መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፎረም**

- የአስተባባሪ ኮሚቴ ሦስት መደበኛ ስብሰባዎች ተካሂደዋል
- በክልላዊ የትብብር መድረክ የሚሳተፉ 5 ተወካዮች ተመርጠው ተሳትፈዋል

3. የዞን ጥምረቶችን በተመለከተ

- በክልላዊ የአጋርነት መድረክ እንዲሳተፉ ተደርጓል
- በ2 ዞኖች ሥልጠና ተሰጥቷል
- በ2 ዞኖች (ደ/ወሎና ምስራቅ ጎጃም) የቴክኒክ እገዛ በመስጠቱ የመንግስት መ/ቤቶች የትብብር ፎረም አቋቁመዋል፡፡

## የኤድስ ፈንድ ማቋቋምና 2% በጀት ማስመደብ ተግባራት ዕቅድ ሪፖርት

| | | የኤድስ ፈንድ ማቋቋም | | | | | | | 2 % ማስመደብ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የአመቱ ዕቅድ | | | የአመቱ ክንውን | | | | ዓመታዊ ዕቅድ ክንውን | | | |
| ተቁ | ዞን /ወረዳ | የመንግስት ሴክተር | የገጠር ቀበሌች | ድምር | የመንግስት ሴክተር | የገጠር ቀበሌች | ድምር | የተሰበሰበ ገንዘብ | የሴክተር መ/ቤቶች ብዛት | 2% የመደቡ ሴክተሮች ብዛት | የተመደበ የበጀት መጠን | ተጨማሪ አስተያየት |
| 1 | ሰሜን ጎንደር | 594 | 578 | 1172 | 46 | 18 | 64 | 54465.8 | 594 | 341 | 441349.37 | |
| 2 | ደቡብ ጎንደር | 240 | 327 | 567 | 182 | 102 | 284 | | 160 | 153 | 162579.00 | |
| 3 | ሰሜን ወሎ | 294 | 299 | 593 | 49 | 3 | 52 | | 294 | 134 | 165551.00 | |
| 4 | ዋግኽምራ | 116 | 125 | 134 | 118 | 0 | 118 | | 112 | 90 | 126423.00 | |
| 5 | ደቡብ ወሎ | 125 | 293 | 418 | 125 | 90 | 215 | | 276 | 187 | 283855.64 | |
| 6 | ኦሮሚያ | 102 | 111 | 142 | 30 | 8 | 38 | | 103 | 80 | 156430.00 | |
| 7 | ሰሜን ሸዋ | 383 | 287 | 670 | 263 | 141 | 404 | | 346 | 257 | 312216.52 | |
| 8 | ምስ/ ጎጃም | 365 | 426 | 794 | 135 | 223 | 358 | 215875.65 | 377 | 307 | 410028.26 | |
| 9 | አዊ | 189 | 179 | 368 | 144 | 61 | 205 | | 189 | 130 | 166731.52 | |
| 10 | ምዕ/ ጎጃም | 354 | 392 | 746 | 216 | 176 | 392 | | 392 | 231 | 458351.40 | |
| 11 | ባህር ዳር | 27 | 7 | 34 | 11 | 0 | 11 | 121621 | 27 | 11 | 146354.00 | |
| 13 | በክልል ደረጃ | 41 | 0 | 41 | 22 | 0 | 22 | | 41 | 20 | 0 | |
| | ድምር | 2830 | 3024 | 5638 | 1341 | 822 | 2141 | | 2911 | 1941 | 2,829,869.71 | |

በበጀት አመቱ በተለያየቱ ቢሮች ደረጃ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግብራት በቢሮ ደረጃ ከዚህ እንደሚከተለዉ ለማቅረብ ተሞክሯል ።

## 1.ትምህርት ቢሮ

- በክልላችን በሚገኙ 718 ት/ቤቶች የማህበረሰብ ውይይት ተካሂዷል፡፡
- 918 ወንድና 847 ሴቶች በድምሩ 1765 መምህራንና ተማሪዎች በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አድርገዋል፡፡
- በክልሉ በሚገኙ 84 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤቶች ለ3 ተከታታይ ወራት ከሴቶች ማህበራት ጋር በመተባበር የፀረ ኤችአይቪ ኤድስ ቅስቀሳ ተካሂዷል፡፡
- የዓለም ኤድስ ቀን በሁሉም ዞኖች የትም/ት ተቋማት ልዩ ልዩ የሕ/ሰብ ክፍሎች ወንድ 201050 ሴት 151550 በድምሩ 322600 በተገኙበት በድራማና በሙዚቃ፣ በሰልፍ ትሪኢት፣ በስነፅሁፍ ዝግጅት ተከብሯል፡፡
- ለ5092 እናት አባት ላጡ ሕፃናት በብር 7925 ዩኒፎርምና ደብተርና እስክሪቢቶ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 2. ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ

- ለ 500 ሰዎች በኮንስትራክሽን ስራ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ አሰሪዎችና ሠራተኞች ኤችአይቪ/ኤድስን በስራ ቦታ መከላከል ስለሚቻልበት ሁኔታ የግንዛቤ ማሳደግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- በኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ በስራ ቦታዎች 5900 ለሚሆኑ አሰሪዎች፣ለሰራተኛና ለማህበራት መሪዎች ግንዛቤ ሊፈጥር የሚችል መመሪያ/ጋይድላይን ብሮሽርስ እና የተለያዩ አይነት ፖስተሮች የማዘጋጀትና የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በክልላችን ለሚገኙ 108 የእድር አመራሮች ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከል የሚያስችል እውቀት እንዲኖራቸው ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- 67 የሚሆኑ ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሴትኛ አዳሪዎች በገቢ ማስገኛ ስራ ሰልጥነው ለዘለቄታ እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

## 3. ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ

- በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች የሚካሄደውን የማህበረሰብ ውይይት መድረኮችን ተከታትሎ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተለይ በሬድዮ/በመካከለኛ ሞገድና በኤፍ ኤም ባህር ዳር/ በሳምንት አራት ቀን ለሁለት ሰዓት ያህል የአየር

ጊዜ በመመደብ እየተሰራ ይገኛል፡፡ይህ በሕ/ሰቡ ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንደፈጠረ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከህብረተሰቡ ከሚሰጡ አስተያየት ለማወቅ ተችሏል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በሳምንት ሁለት ቀን 30 ደቂቃ በመደበኛነት በኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ ፕሮግራም ተላልፏል፡፡

- የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ሴ/ጽ/ቤት ከፋሚሊ ሄልዝ ኢንተርናሽናል ጋር በመተባበር ለኤችአይቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት የቆጋ መስኖ ልማት ተፋሰስ ፕሮጀክት፣ የጣና በለስ ሀይድሮ ፓወር ፕሮጀክትና ከቱሪስት ፍሰት ጋር በተያያዘ ደግሞ ላሊበላ ከተማ ውስጥ የሚኖረውን ህብረተሰብና የፕሮጀክት ሰራተኞችን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ለመታደግና ለመከላከል የሚያስችልን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በመስራት የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ስልጠና በመውሰድ ለቀጣይ ወደ ተግባር ለመግባት የሚያስችላቸውን የ 2001 እቅድ አውጥተዋል፤ የመጀመሪው የህዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር እንዲያስችል በየደረጃው ህብረተሰቡ እየተወያየበት ይገኛል፡፡

## 2.5. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ

በመንግስት በሲቪክ ማህበራት በሐይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም በህብረተሰቡ እየተደረገ ያለውን የፀረ ኤችአይቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ በማገዝና ክፍተቶችን በመሙላት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በክልላችን ውስጥ ከፈተኛ የሆነ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ይኸዉም በሰው ሃይል በገንዘብ በቁሳቁስና በቴክኒክ በሁለም ዘርፍ ማለትም በመከላከሉ በድጋፍና እንክብከቤው እንዲሁም በህክምና አሰጣጥ ላይ አቅም እየፈጠሩልን ይገኛሉ፡፡ በተለይ በድጋፍና ክብካቤ ዘርፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለ20 ወላጅ ያጡ ሕጻናትን ለአሳዳጊዎቻቸዉ የገንዝብ በመስጠት ልጆቹ ትምህርታቸዉን አንዲከታተሉ ተደርጓል ፡፡

- ኤም ኤሰ ኤፍ ወይም ደንበር የለሽ የሕክምና ቡድን የተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በምዕራብ አማራ የከላዛርና የኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ ይስራል፡፡ስለሆነም በአብደራፊ አካባቢ ለሚገኘው 3878 ህብረተሰብ ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ትምህርት ሰጥቷል፡፡ 490 ሰዎችን የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አድርገዋል፤ 168 ሰዎችን ተከታታይ የሆነ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሓኒት እያገኙ ነው፡፡

1. **የመከላከል ተግባራት**

- መረጃ ትምህርትና ስርፀት ስርጭት፣
- ኮንዶም ስርጭት፣
- በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት፣
- ከእናት ወደ ልጅ የቫይረሱን መተላለፍ መከላከል፣

2. **የድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት**

- ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝና ለኤድስ ህሙማን መሠረታዊ ፍላጐቶችን ማሟላትና የገቢ ማስገኛ ተግባራትን እንዲያካሂዱ የአቅም ድጋፍ ለማድረግ፣ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማህበራት በበጀትና በቁሳቁስ መደገፍ፣
- ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናት መሠረታዊ ፍላጎቶችን በማቅረብና የትምህርት ቤት ድጋፍ በማድረግ

3. **የአቅም ግንባታ ተግባራት**

- ህብረተሰቡን መሠረት ላደረጉ ተቋማት የስልጠና፣ የበጀትና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ
- ለፀረ ኤድስ ክበባት የስልጠና፣ የበጀትና ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ

4. **የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር**

- የማህበረሰብ ውይይት አመቻቾችን ማሰልጠንና ለውይይቱ የበጀት ድጋፍ ማድረግ
- የተለያዩ ህብረተሰብ አሳታፊ የሆኑ ዝግጅቶችን ማካሄድ እንዲሁም ድጋፍ ማድረግ ይገኙበታል::

በ2000 የበጀት ዓመት በሁሉም ዞኖች በአጠቃላይ 90 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ረገድ በርካታ ሥራ እያከናወኑ እንደሚገኙ ከየዞኖች የተገኙ ሪፖርቶች ይጠቁማሉ:: እነዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሚያከናውኗቸው ኘሮጀክቶች በርካታ በጀት የሚመድቡ ሲሆን በክልሉ ውስጥ ለሚከናወነው የመከ/መቆጣጠር ተግባር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ::

በየዞኖች ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሚያከናውኗቸው ኘሮጀክቶች ብዛት በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተቁ | ዞን | የመያድ ብዛት | የኘሮጀክት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ባሕር ዳር | 15 | 15 |
| 2 | ደ/ጎንደር | 9 | 9 |
| 3 | ምዕ/ጎጃም | 5 | 7 |
| 4 | ምሰ/ጎጃም | 11 | 20 |
| 5 | ዋግኸምራ | 2 | 4 |
| 6 | ሰ/ሸዋ | 7 | 16 |
| 7 | ሰ/ወሎ | 4 | 10 |
| 8 | አዊ | 2 | 2 |
| 9 | ደ/ወሎ | 18 | 18 |
| 10 | ሰ/ጎንደር | 15 | 15 |
| 11 | ኦሮሞ ብሔረሰብ | 2 | 2 |
| | ድምር | 90 | 118 |

## 3. የአስተዳደርና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ክንውኖች

<u>በሴ/ጽ/ቤት ያለው የሠው ሃይል በዞንና በክልል እንዲሁም በትምህርት ደረጃ</u>

| ተ.ቁ | ዞን/ክልል | የሰው ሀይል | | ድምር | የት/ት ደረጃ | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | | ከዲፕሎማ በታች | ዲፕሎማ | የመጀመሪያ ድግሪ | ሀለተኛ ድግሪ | |
| 1 | ክልል ሴ/ጽ/ቤት | 32 | 11 | 43 | 13 | 12 | 15 | 3 | 43 |
| 2 | ባ/ዳር ልዩ ዞን | 4 | 1 | 5 | 1 | 4 | 0 | 0 | 5 |
| 3 | ምዕ/ጎጃም | 30 | 20 | 50 | 1 | 37 | 12 | 0 | 50 |
| 4 | ምስ/ጎጃም | 38 | 22 | 60 | 5 | 35 | 20 | 0 | 60 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 23 | 13 | 36 | 2 | 29 | 5 | 0 | 36 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | 44 | 23 | 67 | 4 | 55 | 8 | 0 | 67 |
| 7 | ሰ/ወሎ | 22 | 16 | 38 | 1 | 35 | 2 | 0 | 38 |
| 8 | ደ/ወሎ | 40 | 32 | 72 | 9 | 46 | 17 | 0 | 72 |
| 9 | ሰ/ሸዋ | 42 | 29 | 71 | 9 | 51 | 11 | 0 | 71 |
| 10 | አዊ | 18 | 14 | 32 | 0 | 18 | 14 | 0 | 32 |
| 11 | ኦሮምያ | 11 | 1 | 12 | 0 | 11 | 1 | 0 | 12 |
| 12 | ዋግ | 15 | 2 | 17 | 0 | 9 | 8 | 0 | 17 |
| | ድምር | 319 | 184 | 503 | 45 | 342 | 113 | 3 | 503 |

## 4. የክትትልና ድጋፍ ተግባራት

በበጀት ዓመቱ የታቀዱትን ተግባራት ለማሳካት ይቻል ዘንድ በየደረጃው የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ተከናውኗል፡፡ ወቅታዊ የሆነ የመስክ ክትትል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ መፈለግ፣ የስራ አመራርና መደበኛ የኤች አይ ቪ/የኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት ስብሰባዎች፣ የዕቅድ ክንውን አፈፃፀምን መገምገም የመሳሰሉት መደበኛ የሆኑ የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ተከናዉነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በየደረጃው ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት እንዲዘጋጅ የሪፖርት ስርዓትን ለማሻሻል ጥረት ተደርጓል፡፡ በበጀት ዓመቱ ከተዘጋጁት የአፈፃፀም መመሪያዎች አንዱም የክትትልና ግምገማ መመሪያ በመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ከአሁን በፊት ከነበሩት አገልግሎቶች ተጨማሪ መስጠት የሚገባን፣ የነበሩትን አገልግሎቶች በስፋትና ጥራት እንድናካሂድ የሚጠቅሙ አመላካቾችን ያካተተ በመሆኑ ለቀጣይ ስራችን መቃናት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በዚሁ መመሪያ ውስጥ በርካታ የሪፖርት ቅፃቅፆች ተሻሽለው ቀርበው ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን የሪፖርት ስርዓቱ መሻሻል አሰተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራት በዕቅድ እንዲመሩ በየደረጃው የስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች የኤች አይ ቪ/የኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት ጉባዔዎችና የዕቅድ ክንውን ግምገማዎች ተካሂደዋል፡፡

በተጨማሪም የክልሉ ስራ አመራር ቦርድ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱን ተግባራት ለመምራትና መርሃ ግብሮችን እየመረመረ አቅጣጫ ለመስጠት በየወሩ ስብሰባ አድርጓል፡፡ በክልል ደረጃ የ 6 ወር የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በሁለት መድረኮች በደሴና በደ/ማርቆስ የተካሄደ ሲሆን በዚህ መድረክም የ3ኛውን ምዕራፍ የሚሊኔም የፀረ-ኤድስ ዘመቻና የግማሽ ዓመቱን አጠቃለይ ዕቅድ ክንውን ግምገማ ተካሂዷል፡፡ በነዚህ ሁለት መድረኮች የክልሉ ምክር ቤት ከፍተኛ አመራሮች፣ የስራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የሴክተር መ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ተሳትፈዋል፡፡ ለ3ኛዉ ሩብ አመት አፈጻጸም የሚረዱ ከፍተኛ መነሳሳትና የባለቤትነት ስሜት የሚፈጥሩ ውይይቶች በሁለቱ መድረኮች ላይ ተካሄደዋል፡፡ በአጠቃለይ በዉይይቱ መጨረሻ ቀጣይነት ላለዉ የፀረ ኤድስ ሥራ የጋራ የአሰራር አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

ለአብነትም ያህል ፦

- የጤናዉ ሴክተርና ባለሞያዎች በትጋትና በባለቤትነት እንዲንቀሳቀሱ
- የሴክሬታሪት ጽ/ቤቱ የወረዳ ባለሞያዎች በትጋት አንዲሰሩ የወረዳ አስተዳደሮች ከፍተዓ እገዛ እንዲያደርጉ
- የክልል የዞንና የወረዳ አመራር አካላት ሥራዉን ለመምራት ባለቤት መሆን እንዳለባቸዉ
- ሁሉም ኣካለት በመረጃ ኣያያዝና ልዉዉጥ ትኩረት እንዲሰጡ
- በሴክሬታሪት ጽ/ቤቱ የሚመደበዉ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ዉሎ በወቅቱ እንዲወራረድ የሚመለከታቸዉ ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉ ወዘተ ይገኙበታል፡፡

የ9 ወር እቅድ አፈጻጸም ግምገማ በክልሉ ሴክሬታርያት ጽ/ቤትና የዞን ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/ቁጥ/ስራ/ማስ/ጽ/ቤት ሰረተኞች በተሳተፉብት ዉይይት ተደርጎበታል፡፡

የክልሉ ሴ/ጽ/ቤት ለሴክተሮችና ለሌሎች ፈፃሚዎች የሚያደርገውን የበጀት ድጋፎች ክልላዊ ይዘት ያላቸውና በሴ/ጽ/ቤቱ የኘሮጀክት ምዘና ቴክኒክ ኮሚቴ በላይ የሆኑትን ኘ ሮጀክቶች ከተለያዩ የሴክተር መ/ቤት በተውጣጡ የሪቪው ቦርድ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ እያቀረበ ይከታተላል፡፡

ድጋፋዊ የመስክ ጉብኝት ከክልልና ከዞን በየወቅቱ የተደረገ ሲሆን የዞን ማስ/ጽ/ቤቶች እንደየዞናቸው ስፋትና የወረዳዎች ብዛት ተንቀሳቅሰው ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶችና ለፈፃሚዎች ድጋፍ አድርገዋል፡፡

በተለይ የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ የሌሎች ሴክተሮችንና ተቋማትን የሚያሳትፍ በመሆኑ አስተባባሪ ኮሚቴዎችም እንዲሁ ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ ሆነው የዘመቻውን አፈፃፀም እየተከተሉ ይገኛሉ፡፡

በክልሉ ወደ ዞኖችና ወረዳዎች የተደረገን የመስክ ድጋፋዊ ክትትልን በሚመለከት በክልል ደረጃ የተለያዩ ኘሮግራሞችን ለማስተባበርና ክትትል ለማድረግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹም በዞኖች የዕቅድ ክንውን ግምገማዎችና የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት መደበኛ ጉባዔዎች ላይ መገኘትና አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ በዕቅድ የተመራና አሳታፊ ክትትልና ድጋፍ በ 11 ዞኖች መደረጉ ይገኙበታል፡፡ በተካሄዱት ድጋፋዊ ጉብኝቶች ከክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ከዞን አስተዳደር ጽ/ቤቶች፣ ከጤና መምሪያዎች፣ ከወረዳ አስተዳደሮች ከጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች የተገኙባቸዉ ቡድኖች ተሳትፈል፡፡ ቡድኖቹም በሁሉም ወረዳዎች በመገኘት በየዞኖቹ እየተካሄዱ ያሉትን

የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ከማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ የተሻለ አሰራርና ውጤት የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ተሞክሯል፡፡ የ3ኛዉ ምዕራፍ የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘመቻ እንቅስቃሴም ድጋፍ በማድረግ ያጋጠሙ ችግሮችን ከሚመለከታቸዉ ኣካላት ጋር በዉይይት ለመፍታት ጥረት ተደረጓል'

በበጀት አመቱ መጀመሪያ ላይ 9ኛው ክልላዊ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት መደበኛ ጉባዔ ተካሂዷል፡፡ በጉባዔው ላይ የ1999 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቦ ከተገመገመ በኋላ ፀድቋል፡፡ በጉባዔዉ የቀጣዩ በጀት ዓመት ዕቅድ ቀርቦ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ የ2ተኛው ምዕራፍ የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻና የህዝብ ንቅናቄ የተገኙት ውጤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

በክልሉ የሚካሄደዉን የህዝብ ንቅናቄ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለማጠናከር ከሁሉም ዞኖች ለተዉጣጡ ባለሞያዎች የክትትልና ግምገማ የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም በሁሉም ዞኖች ይህ ሥልጠና ለሌሎች ሴክተር መ/ቤቶና የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ባለሞያዎች የመስጠት ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

በክልሉ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት አይነተኛ ምክንያቶችን ለመለየት፣ ለቫይረሱ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆነትን የህብረተሰብ ክፍሎችና ስርጭቱ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰባቸውን አካባቢዎች በመለየት የተሻሉ የመከላከልና መቆጣጠር ስልቶችን ለመተግበር እንደሚረዳ የታመነበት ጥናት በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር/በሲዲሲ-ኢትዮጵያ ድጋፍ በክልላችን ጥናቱ በመጠናቀቅ ላይ ነው፡፡

## 5. የበጀት አጠቃቀምና በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት

የ2000 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀምንና በፋይናንስ ዘርፍ ለተከናወኑ ተግባራት በተደረገዉ የገንዘብ ክፍያ በስራ ላይ የዋለዉን የበጀት መጠን ከዚህ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከለጋሾች 154,716,357.47 ብር የተገኘ ሲሆን ካለፈው ዓመት የተላለፈውን ጨምሮ በዓመቱ በድምሩ ብር 127,667,401 ያህል ለፈፃሚዎች ተላልፎ ሥራ ላይ ውሏል:: የበጀት አፈፃፀሙም 82.46 % ሆኗል፡፡

# 6. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የመፍትሄ ርምጃዎች

## 6.1. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

- በሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ የቁሳቁስ ስርጭት እጥረት
- የህፃናትና ልጆች የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና በሆስፒታል ደረጃ ብቻ መሠጠት የአገልግሎት ተጠቃሚዎች አናሳ መሆን፣
- የፀረ-ኤች አይ ቪ መድኃኒት የጀመሩ ሰዎች ማቋረጥ
- ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል የአገልግሎት ተጠቃሚዎች አናሳ መሆን
- የአገልግሎት ጥራት ማነስ
- በተባበሩት መንግስታት የልማት ፈንድ (UNDAF) የበጀት ፍሰት በተለይ ወደ ወረዳዎች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በኩል መጓተትና ያለመናበብ፣
- የተሽከርካሪ እጥረት በተለይ በዞንና ወረዳ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች፣
- ከፈፃሚ አካላት& ከዞንና ከወረዳ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ጥራቱን የጠበቀና በወቅቱ ሪፖርት መላክ አለመቻል፣
- የማህበረሰብ ውይይት ለማካሄድ የአመቻቾች በወቅታዊ ሥራዎች መጠመድ፣
- የዘመቻዎች መደራረብ

## 6.2. የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች

- የሚሊኒየም ፀረ ኤድስ ዘመቻው በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በታቀደው መልኩ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማድረግ
- የህፃናትና ልጆች የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ህክምና በጤና ጣቢያዎች እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ ይገኛል::
- የበጀት ፍሰትን በሚመለከት ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር ተከታታይ ውይይት እየተደረገ ነው::
- ለፌደራል መ/ቤቶች ጥያቄዎችን በማቅረብ በዘመቻው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስ በተሻለ መጠን እንዲሟሉ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

- ሪፖርት በወቅቱ በማይልኩ ዞኖች በመለየት ችግራቸውን ለመፍታት ተሞክሯል ከዚያ በላይ የሆኑትን በደብዳቤ ተገልፆላቸዋል፡፡
- ሁሉም ዘመቻዎች በእኩል እንዲታዩ ከጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

# 7. የታዩ መልካም የስራ እቅስቃሴዎች

- ከፍተኛ አመራሮች ያደረጉት አመራር በተግባር የሚለውን እውን ማድረጋቸውና ሕዝብን ማንቀሳቀሳ
- የክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ የሥራ አመራር ቦርድ በሪቪው ስብሰባ ላይ በመገኘት አቅጣጫ በመስጠትና ችግሮች ወዲያው መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረጉ
- የተሻለ አሠራሮችን የሚያመጡ የተለያዩ መመሪያዎች ተዘጋጅተው በስራ ላይ እንዲውለ ትውውቅ መደረጉ፣
- በድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት የማህበራት ተሳትፎ ማደግ
- የህዝብ ንቅናቄ ተግባራት ተጠናክረው መቀጠል
- ከአጋርና ረጂ ድርጅቶች ጋር ያለው ትብብርና የኘሮግራሞች አፈፃፀም መሻሻል
- የተጠናከረ ድጋፋዊ ክትትል በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች መደረጉ
- በሚሊኔም የፀረ አች አይ ቪ/ ኤድስ ዘመቻ የአመራሩና የሌሎች በርካታ አጋሮች ተሳትፎና ድጋፍ ማደጉ
- ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ወገኖች ማህበራት በገቢ ማስገኛና የተለያዩ የልማት ሥራዎች በንቃት መሳተፍ
- በሁሉም የክልሉ ቀበሌዎች የዓለም ኤድስ ቀን በዓል በህዝባዊ መድረኮች መከበሩ
- የሕዝቡ የመመርመር ፍላጎት ማደጉና ለመከላከል ተግባር ተስፋ ሰጪ መሆኑ
- የአገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎች መስፋፋት
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ሜይንስትሪሚይንግና ፖረትነርሺኘ አፈፃፀም መሻሻል፣

## 8. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ተከታታይና መደበኛ የሆነ ድጋፋዊ ክትትል መስጠት
- የዞንና የወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶችንና ባለሞያዎች አቅም የማጎልበት ስራ አጠናክሮ መቀጠል
- ለተለያዩ ኘሮግራሞች የመጣን በጀት በወቅቱ ስራ ላይ አውሎ በማወራረድ አፈፃፀምን ማሳደግ
- ከረጂና አጋር ድርጅቶች ጋር ይበልጥ ተቀራርቦ መስራት
- የላቦራቶሪ ቁሳቁስ ሙሉ ፓኬጅ በወቅቱ ማቅረብ
- የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ማስፋፋት
- የባለሙያዎች ስልጠና በስፋት መስጠት
- የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻል
- ሴቶች ላይ ትኩረት መስጠት
- የተጀመረውን ክልላዊ ጥናት ማጠናቀቅ፣ ሌሎች ጥናቶችን መደገፍ
- ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ልውውጥ ማድረግ
- ለሥነ ተዋልዶ ጤና ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ

# ማውጫ


1. መግቢያ ...1
2. ዋና ዋና የተግባራት አፈፃፀም ...3
2.1. መከላከል ...3
2.1.1. የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ...3
2.1.2. መረጃ ትምህርትና ስርፀት ቁሳቁስ ...5
2.1.3. የኤች አይ ቪ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት ...6
2.1.4. ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል ...9
2.1.5. የሚሊኒየም የፀረ ኤድስ ዘመቻ አፈጻጸም ...11
2.1.6. የኮንዶም ትውውቅና ሥርጭት አገልግሎት ...12
2.1.7. የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና የህክምና አገልግሎት መስጠት ...13
2.1.8. የማህበረሰብ ውይይት ...14
2.1.9. ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት መስጠት ...17
ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት ...18
2.2. ድጋፍና ክብካቤ ...18
2.2.1. ቫይረሱ በደማቸው ዉስጥ የሚገኝባቸውና የኤድስ ህሙማን ድጋፍና የማህበራት እንቅስቃሴ ...19
2.2.2. የአለም ምግብ ኘሮግራም ...22
2.2.3. የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት አገልግሎት ...23
2.2.4. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ልጆች የሚደረግ ድጋፍ ...26
2.3. የአቅም ግንባታ ተግባራት ...28
2.4. ሜይንስትሪሚንግና ፖርትነርሽኘ ...37
2.4.1. የመንግስት ሴክተሮች አፈፃፀም ...37
2.4.2. ፓርትነርሽኘ (አጋርነት) ...38
2.5. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ...41
3. የአስተዳደርና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ክንውኖች ...43
4. የክትትልና ድጋፍ ተግባራት ...44
5. የበጀት አጠቃቀምና በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት ...46
6. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የመፍትሄ ርምጃዎች ...47
6.1. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ...47
6.2. የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች ...47
7. የታዩ መልካም የስራ እቅስቃሴዎች ...48
8. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ...49